# ስግደት ፡ ለማን ? ለምን ?

ከቅዱሳት መጻሕፍት በተገኘ መመሪያ መሠረት ቤተክርስቲያናችን በቀኖናዋ ስለ ስግደት አፈጻጸምና ዓይነት ለይታ በየፈርጁ አስቀምጣልናለች ። በመጽሔታችን በቁጥር ፮ ገጽ ፴፱ ላይ የስግደትን ዓይነትና አጠቃቀም ገልጸን ነበር ። ከምሥራቅ ሐረርጌ ከክሕነ ዓመነ የቅሬታ ደብዳቤ ያዘለች ጽሑፍ ደርሳናለች ። ቅሬታውን ለመፋቅ በክርስቲያናዊ መንፈስ ማስረዳት ተገቢ በመኾኑ ከላይ የተጠቀሰውን ርእስ በማስመልከት አንድ በአንድ ለማብራራት እንሞክራለን ።

ጠያቂያችን በጋሻው መኩሪያ " ስንት ዓይነት ስግደት አለ ? ይብራራልኝ " ሲልከተምሮ ማስተማር ሰ/ት/ቤት ያቀረበው መጠይቅ የሰጠነው ማብራሪያ " ስግደት ሁለት ዓይነት ነው ። አንደኛው ለፍጡራን የማይሰጥ ለፈጣሪ ብቻ የሚቀርብ የባሕርይ ወይም የአምልኰት ስግደት የሚባለው ነው ። (ዘፀአት ፳ ፡፩ ፮ ።) ሁለተኛው የጸጋ ወይም የአክብሮት ስግደት ይባላል ። ይህ ዓይነቱ ስግደት ለእመቤታችን ለቅዱሳን መላእክት ለጻድቃን ለሰማዕታት የሚቀርብነው ። እግዚአብሔር ስላከበራቸው ማደሪያው ስላደረጋቸው የጸጋ ወይም የአክብሮት ስግደት ይቀርብላቸዋል ። (ኢያ ፭ ቁ ፲፫ - ፲፭ ። ኢሳ ፵፱ ፡፳፫ ። ዳን ፪ ።፵፯ - ፵፰ ። ራእ. ፫ ፡፰ -፱ ።) የሚል እንደነበር እናስታውስ ።

ከዚህ ቀጥለን በቀጥታ የክሕነ አመነን ጽሑፍ አንድ በአንድ በመመርመር ለቅሬታው መፍቂያ የሚኾን ማብራሪያውን እንቀጥላለን ። አንባቢያን እንዳትቸገሩ የጠያቂውን ጽሑፍ ለብቻ በትምህርተ ጥቅስ በቁጥር በቁጥር እየለየን የእኛን ማብራሪያ እናስከትላለንና ልብ ብላችሁ ተመልከቱ ።

ከጠያቂው ፩ ፡-

በጌታችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ሰላምና ጥበብ ይብዛላችሁ እያልኩ ግንቦት ፹፭ ፩ኛ ዓመት ቁጥር ፮ ገጽ ፴፱ ላይ ስለ ስግደት ለጠያቂ በጋሻው መኩሪያ በተሰጠው መልስ ላይ ቅሬታ ስለተሰማኝ ያለኝን አመለካከት በማስረጃ በማስደገፍ እነሆ ልኬላችኋለሁ ለማማማሪያ ወይም ለውይይት እንዲረዳ በቀጣይ መጽሔቷ ላይ እንዲወጣ በጌታ ስም እጠይቃችኋለሁ ።

መልእክቴን በሙሉ በታማኝነት እንደምታወጡት አልጠራጠርም ።

ወንድማችሁ
ክሕነ ዓመነ
ከምሥራቅ ሐረርጌ ።

ከአዘጋጆች - ፩ ፡- አሜን ይሁንልን ይደረግልን ! !ለአንተም ማስተዋሉንና ጥበቡን ያድልህ ለመማማሪያ ለውይይት እንዲረዳ በፈጣሪያችን ስም ስለጠየቅኸን መልእክትህን በታማኝነት አውጥተናታል ። ስሕተት ካለ ለመታረም መዘጋጀት ከሁላችንም ይጠበቃል ። በስሕተታዊ ሐሳብ ጸንቶ እንደፈሪሳውያን ለክርክር ብቻ ጌታን ለመሞገት ጥያቄ ማቅረብ ግን እነርሱን መምሰል ስለሚኾን እውነትን ላለመቀበል ከሚያረግ እልከኝነት ይጠብቅህ ይጠብቀን ።

ከጠያቂው - ፪ "በእርግጥ መላእክትና ቅዱሳን ይሰገድላቸዋል?"

ከአዘጋጆች -፪- "አዎን ይሰገድላቸዋል። የሚቀርብላቸውም ስግደት የአምልኮት ወይም የባሕርይ ስግደት አይደለም ። የአክብሮት ወይም የጸጋ ስግደት ግን ይቀርብላቸዋል ። ምክንያቱም መላእክትና ቅዱሳን ከእግዚአብሔር የተሰጣቸው ክብርና ጸጋ አለ ። እግዚአብሔር የወደደውን መውደድ ጸጋ ክብር ሰጥቶ ያከበረውን ማክበር ይገባል ። መላእክትና ቅዱሳንን እንደ ጣዖታትና በጣዖታት ላይ እንዳደሩ የሐሰት አማልክት አጋንንት (ርኩሳን መናፍስት) መቁጠርና ማቃለል ክርስቲያናዊ አስተሳሰብ አይደለም ። ከአንድም ሥፍራ ከመጽሐፍ ቅዱስ ለዚህ ስሕተታዊ አስተሳሰብ ማስረጃ አይገኝም ።

በአጸፋው ግን እግዚአብሔር የመረጣቸው ፣ ያከበራቸው ቅዱሳን የጸጋ አማልክት እንዲሆኑ ሥልጣን ተሰጥቷቸዋል ። የጸጋ ጌትነት ፣ የጸጋ አምላክነት አላቸው ለዚህም ዋቢያችን መጽሐፍ ቅዱስ መሆኑን ፣ ስናበስር ለደስታችን ወደር የለውም።

እግዚአብሔር ጌትነት አምላክነት ፣ ንጉሥነት የባሕርይ ገንዘቡ ሲሆን ለመላእክትና ለቅዱሳን ግን በጸጋ የተሰጣቸው ክብር ነው ። በጸጋ የአምላክነት ፣ የጌትነት ፣ የንጉሥነት ክብር መስጠታቸውን ካወቅን የጸጋ ወይም የአክብሮት ስግደት አይቀርብላቸውም ለማለት አይቻለንም ።

ሀ) "እግዚአብሔርም ሙሴን አለው ፡- እይ እኔ ለፈርዖን አምላክ አድርጌሃለሁ ፤ ወንድምህም አሮን ነቢይ ይሆንልሃል' (ዘጸአ. ፯ ቁ. ፩) ።

ሙሴ የባሕርይ አምላክ ነውን ?' ወንድሙ አሮንስ ለሙሴ ነቢይ እንዴት ሆነለት? ተመልከት! ማስተዋሉን ይስጥህ ! ከቅዱሳን ነቢያት አንዱ ለሆነው ለሙሴ እግዚአብሔር የጸጋ አምላክነትን (ጌትነትን) እንደአጎናጸፈው አየህን? እንግዲህ እንደ ሙሴ ላሉት ቅዱሳን የጸጋ ክብር ከተሰጣቸው ስለ ተሰጣቸው ጸጋ (ክብር) የጸጋ ስግደት (የአክብሮት ስግደት) ቢቀርብላቸው ለጣዖት ወይም ለአጋንንት እንደቀረበ ክብር ተደርጎ ክርስቲያኖችን መተቸት መዝለፍ ይገባልን? አይገባም

ለ) "ሙሴም ኢትዮጵያይቱን አግብቶአልና ባገባት በኢትዮጵያይቱ ምክንያት ማርያምና አሮን በእርሱ ላይ ተናገሩ ። እነርሱም በውኑ እግዚአብሔር በሙሴ ብቻ



www.ethiopianorthodox.org

ተናግሮአልን? በእኛስ ደግሞ የተና ገረ አይደለምን? አሉ ፤ እግዚአብ ሔርም ሰማ ። ሙሴም በምድር ላይ ካሉት ሰዎች ሁሉ ይልቅ እጅግ ትሑት ሰው ነበረ ።. . .በባሪያዬ በሙሴ ላይ ትናገሩ ዘንድ ስለምን አልፈራችሁም? አለ ። እግዚአብሔ ርም ተቆጥቶባቸው ሄደ ። . . .''
(ዘኁል. ፲፪ ቁ. ፩—፲፩።)

የሙሴ እህት ነቢይት ማርያምና ወንድሙ ካህኑ አሮን ሙሴን ስላቃለሉት ከሙሴ የብቃት ደረጃ ሳይደርሱ በራሳቸው ሐሳብ በቅ ተው ከሙሴ የምናንስበት ምክንያት የለም ስላሉ የሙሴን የጸጋ ክብር ተረድተው በሙሴ አማላጅነት ምሕረት እስኪያገኙ ድረስ በእግዚ አብሔር አምላክ የመዓት ጨንገር ተገርፈዋል ። የተሰጠውን ጸጋ ዐው ቀው ተገቢውን ክብር በሰጡት ጊዜ ግን ይቅርታን (ስርየተ ኃጢአ ትን) አግኝተዋል ። ዛሬስ ቢሆን የጸጋ አማልክት የተባሉ መላእክት ንና ቅዱሳንን ስለማክበር ወይም የአክብሮት ሰጊድ አይገባቸውም የሚሉ ከቁጣው እንዴት ያመል ጣሉ? ሊያመልጡ አይችሉም ።! ለምን ቢባል ትዕቢት ነውና ወይም ምቀኝነት ። በትዕቢትና በምቀኝነት የሚገኝ አንዳችም ጸጋ የለም ። ቅዱስ ጴጥሮስ ያስተማረንን እንይ ''እንዲሁም ጎበዞች ሆይ ለሽማግ ሌዎች ተገዙ ፤ ሁላችሁም እርስ በርሳችሁ እየተዋረዳችሁ ትሕትናን እንደ ልብስ ታጠቁ ፤ እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ይቃወማልና ለት ሑታን ግን ጸጋን ይሰጣል ።'' (፩ኛ ጴጥ. ፭ ፥ ቁ. ፭) ቅዱሳንን ማክ በር በምድርም በሰማይም በሥጋም በነፍስም ጸጋን ይሰጣል ። ኢያሱ ሙሴን ፤ ኤልሳዕ ኤልያስን ቢያከ ብሩ በሙሴ ያደረ ጸጋ ለኢያሱ በኤልያስ ያደረ ሀብት (መንፈስ) ለኤልሳዕ እንደተሰጠ ማስተዋል ይጠቅማል ። የክርስቶስን መልዕክተ ኞች ቅዱሳንና መላእክትን ብናከ ብራቸው በረድኤታቸው እንደምን ጠቀም አንጠራጠር ። ክብራቸውን ለመግለጽ የተሰጣቸውን ጸጋ በመ ረዳት የጸጋ አማልክት እንደመሆ ናቸው የጸጋ ወይም የአክብሮት ሰጊድ እናቀርብላቸዋለን ይኸን በማድረጋችን አልተሳሳትንም አም ልኮተ እግዚአብሔርን ቀምተን ለፍጡራን እንደሰጠን ሊቆጠር ብንና ሊገመት አይገባም በጠባብ አመለካከት ሳይሆን የአስተሳሰብ አድማሳችንን በመጽሐፍ ቅዱስ መነጽርነት ተረድተን ሰፋ አድር ገን እንመልከተው ። ለዚሁም እግ ዚአብሔር ይርዳን አሜን ። (ዘዳግ. ፴፬ ፥ ፱—፲ ። ፪ ነገሥ. ፪ ፥ ፯—፲፬። ማቴ. ፲ ፥ ፵—፵፩)

ሐ) የጸጋ አምላክነት የተሰጠው ለሙሴ ብቻ አይደለም ። ለቅዱሳን ሁሉ ይኸ መብት አልተነፈጋቸ ውም ። (ዮሐ. ፲ ፥ ቁ. ፴፬—፴፮ ። መዝ. ፹፩ ፥ ቁ. ፯ ) ሙሴ ራሱ በኦ ሪት ዘዳግም ምዕ. ፲ ። ከቁጥር ፲፯— ፲፰ መላእክትም ሆነ ቅዱሳን የጸጋ አማልክት የጸጋ ጌቶች መባላቸውን ገልጾ የእነርሱ አምላክ የእነርሱ ጌታ እግዚአብሔር ጌትነቱ አምላ ክነቱ የባሕርይ መሆኑን አልሰወ ረም ። 'የአማልክት አምላክ የጌቶች ጌታ' ማለት ትርጓሜው ከላይ እንደ ተገለጸው ነውና ። ሎጥ ሁለቱን መላእክት እንግድነት ሲቀበላቸው ፊቱን ደፍቶ ወደ ምድር ከሰገደ በኋላ ጌቶቼ ሆይ ወደ ባሪያችሁ ቤት አቅኑ ብሎ ተቀብሏቸዋል ። በዚህም ለመላእክት የጸጋ ጌትነት እንዳላቸውና የጸጋ ስግደትም እንደ ሚቀርብላቸው እንማራለን ። መላ እክቱም ሎጥ አለመሳሳቱን ተረድ ተው ድርጊቱን አልተቃወሙም። መልአክነታቸውን የተረዳው ዘግይቶ ቢሆንም በእግዚአብሔር ስም የሚ መጣውን እንግዳ መቀበል ማለት ራሱን እግዚአብሔርን እንደመቀ በል አድርጎ በመቁጠሩ ተመስገነ በት እንጂ አልተነቀፈበትም ። (ዘፍጥ. ፲፱ ፥ ፩—፫)። ሎጥና ቤተሰቡ መላእክትን እንደተቀበሉ በምሥጢር ሲያመለክት ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ብሏል ። ''የወንድማማች መዋደድ ይኑር ። እንግዶችን መቀበል አት ርሱ ፤ በዚህ አንዳንዶች ሳያውቁ መላእክትን እንግድነት ተቀብለዋ ልና ።'' (ዕብ. ፲፫ ፥ ቁ. ፩—፪።)

ሎጥ በሰዎች አምሳል የተገለጹ ለትን መላእክት እንግድነት ሲቀበ ላቸው በትሕትና ከመሬት ተደፍቶ እየሰገደ 'ጌቶቼ' በማለት መሆኑን



የጌታን መወለድ በመስማት ለባሕርይ አምላክ ለኢየሱስ ክርስቶስ እረኞች ሲሰግዱ



www.ethiopianorthodox.org

ከተረዳን ዘንድ እኛም እንደ ሎጥ ቅዱሳንን ፣ መላእክትን ብናከብራቸው ምን የሚጐድልብን ክብር አለ? የምንቃወምበትስ ምክንያት ምንድነው? በእርግጥ ቅንዓት ሰይጣናዊ ወይም ትዕቢት ካደረብን እንድንቃወም ያደርገናል ። ይኸም ባይሆን አለማወቅ ፣ አለመጠንቀቅ ከዚህ ስሕተት ሊያደርስን ይችላል ።

ነቢዩ ዳዊት እግዚአብሔርን "አቤቱ በድንኳንህ ውስጥ ማን ያድራል? በተቀደሰውም ተራራህ ማን ይኖራል?" ብሎ ላቀረበው ጥያቄ በድንኳን ፣ በተቀደሰ ተራራ በተመሰለችው ሰማያዊት ድንኳን በደብረ ጽዮን መንግሥተ ሰማያት ለመኖር ከሚያበቁ መስፈርቶች (መንፈሳዊ የትሩፋት መመዘኛዎች) አንዱ እግዚአብሔርን በማምለክ በሕግ በአምልኮ ጸንተው የሚኖሩትን ፈሪሃ እግዚአብሔር ያላቸውን ቅዱሳንን ማክበር እንደሆነ ከመንፈስ ቅዱስ መልስ አግኝቷል ። እግዚአብሔርን የሚፈሩትን የሚያከብር ለዘላለም በነፍስም በሥጋም እንደማይታወክ ተገልጾለታል ። (መዝ. ፲፬(፲፭) ቁ. ፩—፭።)

በብሉይም በሐዲስም ለቅዱሳን ክብር መስጠት እንደሚገባ የተጻፈውን ተገንዝበን የጸጋ ስግደት እናቀርብላቸዋለን ። በቃልም በሁኔታም ክብራቸውን እንገልጻለን ። በዚህም ተግባራችን እንጠቀምባታለን እንጂ አንጎዳበትም ። ጥንታውያን ክርስቲያኖች ሐዋርያትን በማክበራቸው ባለመዳፈራቸው ያገኙትን ጠቀሜታ እናስተውል ። (የሐዋ. ሥራ ፭ ፣ ቁ. ፲፪—፲፯ ።)

ከጠያቂው - ፫ - "በቅድሚያ በጌታ ስም ሰላምና ጥበብ ይብዛላችሁ ። እላለሁ" ። ግንቦት ፹፭ ዓ.ም. ፩ኛ ዓመት ቁጥር ፯ ገጽ ፴፱ ላይ ስግደት ለጠያቂ በጋሻው መኩሪያ የተሰጠው መልስ ፦

"ሁለተኛው ስግደት የጸጋ ወይም የአክብሮት ስግደት ይባላል ይህ ዓይነቱ ስግደት ለእመቤታችን፣ ለቅዱሳን መላእክት ፣ ለጻድቃን ፣ ለሰማዕታት የሚቀርብ ነው ። እግዚአብሔር ስላከበራቸው ማደሪያው ስላደረጋቸው የጸጋ ወይም የአክብሮት ስግደት ይቀርብላቸዋል ።" ይላል ።

ለዚህም ማረጋገጫ ከመጽሐፍ ቅዱስ የተሰጡ ጥቅሶች ፣

ኢያ ፭ ቁ ፲፫—፲፭ ። ኢሳ ፵፱ ፣ ቁ ፳፫ ። ዳን ፪ ፣ ፵፮—፵፯ ። ራእይ ፫ ፣ ፰—፱ ናቸው ። እስቲ እነዚህ ጥቅሶች ይህን ያረጋግጡ እንደሆነ በየተራ እንመልከታቸው?

፩ኛ/ ኢያ፣፭፣ቁ፲፫-፲፭ የተመዘዘ ሰይፍ የያዘ ሰው በኢያሱ ፊት ቆሞ ነበር . . . እርሱም "የእግዚአብሔር ሠራዊት አለቃ ሆኜ አሁን መጥቻለሁ ። " አለ ። ሰይፉ ይዞ የቆመው በእርግጥ ሰው ነበርን ? ከኢያሱ ወገንም ሆነ ጠላት አለመሆኑን ገልጾአል ፤ እግዚአብሔር በተለያየ መልክና ምሳሌ እራሱን መግለጹን ዕብ ፩፣፩-፪ በአስረጅነት በመጥቀስ በዚህ መጽሔት ተጠቅሷል ፤ ሰይፍ ይዞ በኢያሱ ፊት በኢያሪኮ ምድር የቆመው እራሱ ወገንህም ጠላትህም አይደለሁም ፣ ግን የእግዚአብሔር ሠራዊት አለቃ ሆኜ አሁን መጥቻለሁ ያለው በውኑ ሰው ነው ? ከሆነ ማነው ? ወይስ ሰው መስሎ የመጣ መልአክ ይሆን ? ለዚህስ ምን ማስረጃ ይኖረናል ? በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ መላእክት እራሳቸውን በማሳወቅ ሲገልጹ ብዙ ቦታ ይነበባል ትክክለኛው ግን ሰይፍ ይዞ ኢያሱን ያናገረው የእግዚአብሔር ሠራዊት አለቃ እራሱ የሠራዊት አምላክ እግዚአብሔር እንጂ ሰው ወይም መልአክ አይደለም ። . . . .

ከአዘጋጆቹ፦ ፫ . . . እኛም በአጠፌታው ሰላምና ጥበብን እንመኝልሃለን ። ሰይፍ ይዞ የቆመው በእርግጥ ሰው ነበርን ? ብለህ ለጠያቅኸው ምላሹ አይደለም ነው ። በመጽሔታችንም ሰው ነበር አላልንም። ሰው መስሎ የመጣ መልአክ ይሆን ለዚህስ ምን ማስረጃ ይኖረናል ? ላልከውም መልሱ አዎን መልአክ ነው ። መላእክት ሰው መሰለው መታየት ይችላሉ ። ማስረጃውም አንደኛ ኢያሱ ፭ ቁ ፲፫ -፲፭ ያለው ሲኾን ኹለተኛውም በዘፍጥ ፲፰ ቁ ፳፪ ላይ "ሰዎቹም ከዚያ ፊታቸውን አቀኑ ወደ ሰዶምም ሄዱ አብርሃም ግን በእግዚአብሔር ፊት ገና ቆሞ ነበር " ይላል በቁጥር ፳፪ በሰዎች አምሳል የተገለጡት በዘፍጥ ፲፱ ቁ ፲፪ ላይም "ሁለቱም ሰዎች ሎጥን አሉት ከዚህ ሌላ ማን አለህ ? . . . " ተብሎ የተነገረላቸው በዘፍጥ ፲፱ ቁ ፩-፪ ላይ ሁለቱም መላእክት በመሸ ጊዜ ወደ ሰዶም ገቡ ሎጥም በሰዶም በር ተቀምጦ ነበር ሎጥም ባያቸው ጊዜ ሊቀበላቸው ተነሣ ፊቱንም ደፍቶ ወደ ምድር ሰገደ ፦ አላቸውም ጌቶቼ ሆይ ወደ ባሪያችሁ ቤት አቅኑ ከዚያም እደሩ . . . ብሎ የጸጋ ወይም የአክብሮት ስግደት በማቅረብ በትሕትና የተቀበላቸው መላእክት በሰው አምሳል ተገልጸውለታል ። ስለዚህ የእግዚአብሔር ሠራዊት አለቃ የኾነው መልአክ ለኢያሱ ሰይፍ ይዞ በሰው አምሳል ተገለጸለት እንላለን ። ንባቡም የሚያስረዳን ይኸንኑ ነው ። አንተ እንዳልከው እግዚአብሔር በዕብ ምዕ ፩-ቁ ፩ና ፪ ላይ በተጠቀሰው መሠረት በብዙ ዓይነት ምሳሌ ራሱን ይገልጻል የእኛም እምነት ይኸው ነው ዳሩ ግን "የእግዚአብሔር ሠራዊት አለቃ ሆኜ መጥቻለሁ ያለውን ይዘህ ራሱ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ነው ማለት ያልተነበበ መተርጐም ነው መጽሐፉ እንዲህ አላለም ። ምናልባት የሠራዊቱ አለቃ (መልአኩ) ሰይፍ በመያዙ እግዚአብሔር ነው ብለኸው እንደኾነ ተሳስተሃል ። መላእክት ሰይፍ ይዘው የማይገለጹ አይምሰልህ ። ሰይፍ ይዘው ይገለጻሉ ።

በኦሪት ዘኊልቊ ምዕ ፳፪፣ቁ ፴፩ ። ላይ "እግዚአብሔርም የበለዓምን ዓይኖች ከፈተ ፤ የእግዚአብሔርን መልአክ በመንገድ ላይ ቆሞ የተመዘዘም ሰይፍ በእጁ ይዞ አየ ሰገደም በግንባሩ ወደቀ" ይላል ። ሰይፍ ይዞ ለበለዓም የተገለጸለትና በለዓምም የጸጋ ሰጊድ ያቀረበለት ማን ይመስልሃል ? እርሱም የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ነው ትለው ይኾን ? የእግዚአብሔር መልአክ እግዚአብሔር ነው አይባልም ። የእግዚአብሔር መልእክተኛ ወይም መልከተኛ ወይም መልአክ እግዚአብሔር ይባላል እንጂ ። በለዓም ለመልአኩ መሰገዱ ለጣዖት እንደቀረበ ስግደት ይቆጠራል የምትል ከኾነ መልአኩንም እንደጣዖት አድርገህ መቁጠርህን ተገንዘብ ። ወይም ደግሞ መልአኩም መመለክ እንደሚፈልግ ዓይነት እንደገመትኸው አስተውል መልአኩ በለዓም ስለሰገደለት ለምን

www.ethiopianorthodox.org

ሰገድህልኝ ብሎ ይኸን እንደጥፋት አልቆጠረበትም አህያይቱን በጭካኔ በመደብደቡና ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጭ እግዚአብሔር ያልረገመውን ሕዝብ ለመራገም በማሰቡ ግን ወቅሶታል ። በለዓምም መልአኩን ይቅርታ ጠይቆ መመሪያ ተቀብሏል ። መመሪያውን ለወደፊት እስኪያፈርሰው ድረስ ለጊዜው ታዛዥነቱን ገልጿል ። ከዚህ ጋር በተጨማሪ ልታስተውለው የሚገባህ ነገር አለ ። መላእክት እንደ ሰይጣን (ዲያብሎስ) የፈጣሪያቸውን የባሕርይ ክብር የሚዳፈሩ ወይም እንደ ዛርና ቆሌ እንደ ሠራዊተ አጋንንት መመለክ የማይሹ መኾናቸውን ተገንዝበህ የጸጋ ክብር (ሰግደት) በቀረበላቸው ጊዜ ኹሉ ዝም ብለው በመቀበላቸው መመለክን እንደፈለጉ አድርገህ አትጠራጠራቸው ። ቅዱሳን መላእክት ከእንዲህ ዓይነት ከንቱ ግብር የራቁ የእግዚአብሔር አገልጋዮች ፈቃድ ፈጻሚዎች ናቸው በዚህ ቅሬታ አይገባም ።

''የእግዚአብሔር ሠራዊት አለቃ ሆኜ መጥቻለሁ ያለውን ቃል እንመርምር ይህ ቃል የሚያመለክተን ለእግዚአብሔር ሠራዊት እንዳሉት ነው ። የእግዚአብሔር ሠራዊት የሚባሉት እነማን ናቸው ብንል በዚህ አገባብ ሠራዊት የተባሉት መላእክት ናቸው ። የእግዚአብሔር ሠራዊት ብንል ወይም የእግዚአብሔር መላእክት ብንል ፍቹ ያው ነው ። መላእክት ማለት ነው ። መላእክት የእግዚአብሔር ሠራዊት (ጭፍሮች ወታደሮች) ወይም መልእክተኞች ናቸው ። በመጽሐፍ ቅዱስ ሠራዊት የሚለው ቃል ብዙ ትርጉም ቢኖረውም በዚህ አገባብ ግን ስለ መላእክት ያመለክታል ። እስቲ ለዚህ አባባላችን መጽሐፍ ቅዱሳዊ መረጃዎችን እናጢናቸው ።

ሀ) "ሰማይና ምድር ሠራዊታቸውም ሁሉ ተፈጸሙ "(ዘፍጥ· ፪፡ቁ፡፩ ። ) ሠራዊታቸውም ሲል ፍጥረታት ተብሎ ይተረጐማል የመላእክትን ፀሐይ ጨረቃ ከዋክብትን አዝርዕት አትክልት ዕፀዋትን እንስሳት አራዊት አዕዋፍን ሰውን ጭምር የሚያጠቃልል ቃል ነው ።

ለ) "በዚያም ዘመን አቤሜሌክ ከሙሽራው ወዳጅ ከአኮዘትና ከሠራዊቱ አለቃ ከፊኮል ጋር አብርሃምን አለው በምታደርገው ሁሉ እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ነው ። " (ዘፍጥ፡፳፩፡ቁ ፳፪ ። ) ፊኮል የሠራዊት አለቃ ተብሏል እዚህ ላይ ሠራዊት የተባሉት ወታደሮች ናቸው ። ፊኮል የወታደሮች አለቃ ወይም የጭፍሮች አለቃ መኾኑ ነው ። በዘመናዊ አነጋገር ኮሎኔል ጄነራል ማርሻል እንዲሉ እንደዚያ ማለት ነው ።

ሐ) "ሠራዊቱ ሁሉ ፈቃዱን የምታደርጉ አገልጋዮቹ እግዚአብሔርን ባርኩ" ይላል ። (መዝ፻፫ቁ፳፪) ሠራዊቱ ሲል መላእክቱ ሁሉ ሲል ነው አገልጋዮቹ ሠራዊቱ መላእክት የእግዚአብሔር ፈቃድ ፈጻሚዎች ናቸው ። ፈጣሪያቸውንም ሲያመሰግኑ ይኖራሉ ይኸም ኃይለ ቃል ከዕብ ፩ቁ፯ ጋር ተመሳሳይና ተዛማጅ ነው ስለ መላእክትም መላእክቱን መናፍስት አገልጋዮቹንም የእሳት ነበልባል የሚያደርግ ይላል" (መዝ፻፫ ቁ፬) መላእክት አገልጋዮች ተብለዋል የተባሉ ሠራዊትም መላእክት መኾናቸው በዚያ ይታወቃል ። የእግዚአብሔር ሠራዊቲት ማለትና የእግዚአብሔር መላእክት ማለት አንድ ነው ብለን ነበር የዚህ ማስረጃም በዕብ ፩ ቁ ፮ና በመዝሙር ፺፮ ፯ ላይ የተጠቀሰው "የእግዚአብሔር መላእክት ሁሉም ለእርሱ ይሰግዱ " ያለው ቃል ነው በተጨማሪም ዳዊት መላእክቱ ሁሉ አመስግኑት ሠራዊቱ ሁሉ አመስገኑት " ይላል ። (መዝ፻፵፰ ቁ፪ ) መላእክት ማለትና ሠራዊት ማለት ተመሳሳይ ነው ።

እንዲህ ከኾነ የእግዚአብሔር ሠራዊት አለቃ ማለትና የእግዚአብሔር መላእክት አለቃ ማለት ልዩነት እንደሌለው እናያለን ።

መጽሐፍ ቅዱሳችን "የጭፍሮች አምላክ እግዚአብሔር " የሠራዊት አምላክ እግዚአብሔር ወይም የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር በሚል ቅጽል ስለ እግዚአብሔር ይገልጻል ትርጉሙ የመላእክት ፈጣሪያቸው ማለት ነው (መዝ ፳፫ ቁ ፲ ኢሳ፮ቁ፫)

ከላይ እንደተገለጸው የእግዚአብሔር ሠራዊት አለቃ ማለትና የእግዚአብሔር መላእክት አለቃ ማለት አንድ ነው ካልን የእግዚአብሔር ሠራዊት ( መላእክት ) አለቃ ማነው ብለን መጠየቅ ሊኖርብን ነው ። የሠራዊት (የመላእክት) አለቃ የተባለው አልቅናው ለእግዚአብሔር ሠራዊት (መላእክት) መኾኑ ታውቋል እግዚአብሔር ሠራዊት (መላእክት) አሉት ፤ ለመላእክቱ (ለሠራዊቱ) አለቃ ሾሞላቸዋል ለእግዚአብሔር ሠራዊት ወይም መላእክት አለቃቸው በማዕረግ በክብር ከእነርሱ የላቀ መልአክ ነው እንጂ ራሱ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዳልሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ራሱ ይመሰክርልናል መረጃዎቹንም እንደሚከተለው አንድ በአንድ እናቀርባቸዋለን በማስተዋል እንመልከታቸው ።

ለኢያሱ የተገለጸለት የእግዚአብሔር ሠራዊት (መላእክት) አለቃ እግዚአብሔር ካልኾነ እንግዲያማ ማነው ቢባል መልሱ ቅዱስ ሚካኤል ነዋ ሌላ ማነው ተብሎ ይመለሳል በውኑ ቅዱስ ሚካኤል ለእግዚአብሔር ሠራዊት (መላእክት) አለቃቸው ነውን ?

ሀ( "በዚያን ዘመን ስለ ሕዝብህ ልጆች የሚቆመው ታላቁ አለቃ ሚካኤል ይነሣል፣ . . " ይላል (ዳን፡ ፲፪፡፩ ። ) ሚካኤል አለቃ ብቻ ሳይሆን ከአለቃም አለቃ ታላቅ አለቃ መኾኑ ተገልጿል የማን አለቃ ነው እንዳይባል ሚካኤል መልአክ ነው የመላእክት ሁሉ አለቃ መኾኑን እንረዳለን ።

ለ) "ከዋነኞቹ አለቆች አንዱ ሚካኤል ሊረዳኝ መጣ " (ዳን ፲ቁ፲፫) ሊቃነ መላእክት አሉ የእነርሱ ጠቅላይ አለቃ ሚካኤልነው ። ለዳንኤል ተገልጾ የሚካኤልን አልቅናና ተረዲኢነት የነገረው ግሩም መልአክ ነው ከቁጥር ፩-፳፩ ብንመለከት መልአክ መኾኑን እናውቃለን ።

ሐ) "በዚህም ነገር ከአለቃችሁ ከሚካኤል በቀር ማንም የሚያጸናኝ የለም ። " (ዳን ፲፡ቁ፳፩ ። ) ይላል ። ለነቢያትም አለቃ ኾኖ ሲመራቸው ኖሮዋል እነርሱም አለቃቸውን ሲያከብሩ ሲከተሉ ነበር ። ሚካኤል መልአኩን ሳይቀር ለማጽናት ጸጋ የተሰጠው አለቃ መኾኑን የሚያስገነዝበን ኃይል ቃል ነው ። ስሙ ባይገለጽም

ሚካኤል የነቢያት መሪ ኾኖ የእግዚአብሔር ሰዎች ሲረዳቸው እንደነበር ይኸን ጥቅስ መሠረት በማድረግ ከእነ ሙሴ ጀምሮ ብንመረምር አለቅነቱን በሁሉም ዘርፍ እናረጋግጣለን ።

www.ethiopianorthodox.org

መ) “ በእስራኤል ሠራዊት ፊት
ይሄድ የነበረው የእግዚአብሔር መል
አክ ፈቀቅ ብሎ በኋላቸው ሄደ . .
(ዘጸአ ፲፬፥ቁ፲፱ ) የነቢያትና የእስራ
ኤል ሠራዊት አለቃ ሚካኤል መኾ
ኑን ለማስረዳት ያ ግሩም መልአክ
ለነቢዩ ዳንኤል እንደነገረው ተጠ
ቅሷል ከዚህ ላይ ከፊት እየመራ
ከኋላ እየጠበቀ ሙሴንና የእስራኤ
ልን ሠራዊት ሲመራ ሲረዳ የነበረው
መልአክ ስሙ ሚካኤል ተብሎ ባይ
ጠቀስም መጋቤ ብሉይ መኾኑ ስለ
ታወቀ “አለቃችሁ ” ባለው አነጋገር
ያለ ጥርጥር ቅዱስ ሚካኤል መኾኑን
እናምናለን ።

ሠ) “በመንገድ ይጠብቅህ ዘንድ
ወደዘጋጀሁትም ስፍራ ያገባህ ዘንድ
እነሆ እኔ መልአክት በፊትህ እሰድዳ
ለሁ ። በፊቱ ተጠንቀቁ ቃሉንም
አድምጡ ስሜም በእርሱ ስለኾነ
ኃጢአት ብትሠሩ ይቅር አይልምና
አታስመርሩት አንተ ግን ቃሉን ብት
ሰማ ያልሁህንም ሁሉ ብታደርግ
ጠላቶችህን እጠላቸዋለሁ የሚያስጨ
ንቁህም አስጨንቃቸዋለሁ መልአኬ
በፊትህ ይሄዳልና . . . ወደ ኢያቡሳ
ውያንም ያገባሃል ፤ እኔም አጠፋቸዋ
ለሁ ” (ዘጸአ ፳፫ ቁ ፳-፳፫ ). እስራ
ኤልን ሲጠብቅ ሲመራ የነበረው
ከነቢዩ ሙሴ ያልተለየው ተራዳኢው
መልአክ “አለቃችሁ ” የተባለው
ቅዱስ ሚካኤል መኾኑን እናስተውል
ሙሴ ከሞተ በኋላ እግዚአብ
ሔር ለኢያሱ ተገልጾ “ከሙሴ ጋር
እንደሆንሁ እንዲሁ ከአንተ ጋር እሆ
ናለሁ አልጥልህም አልተውህም፤”
ብሎ ቃል ገብቶለታል (ኢያሱ ፩፡፭
-፮ ።) እንግዲህ ከሙሴ ጋር የነበረው
ታላቅ አለቃ ሚካኤል ከኢያሱ ወልደ
ነዌ ጋርም እንደሚኾን በቃል ኪዳኑ
መረዳት ይቻላል በዚህ ቃል ኪዳን
መሠረት ነበር የእግዚአብሔር ሠራ
ዊት ( መላእክት ) አለቃ ሚካኤል
ሰይፍ ይዞ በኢያሪኮ ለኢያሱ የተገ
ለጸለት ።

“ጌታችን ከሰማይ ይወርዳልና
በሊቀ መላእክት ቃል በእግዚአብሔር
መለከት ድምፅም ያዝዛል ፤ አስቀድሞ
የሞቱ ሙታንም በክርስቶስ ይነሣሉ”
(፩ ተሰሎ ፬፥ቁ፲፮።) ይላል ።

በዕለተ ምጽአት ጌታችን ለፍርድ
ሲገለጽ አብሮ የሚመጣው አዋጁን
የሚያሰማው የመላእክት አለቃ የተ
ባለው ሚካኤል ነው ሚካኤል የመ
ላዕክት አለቃ መኾኑን በይበልጥ ለመ
ረዳት “ የመላእክት አለቃ ሚካኤል
ግን . . . ጌታ ይገሥጽህ አለው” ። ያሉ
ውንም “ሚካኤልና መላእክቱም ዘን
ዶውን ተዋጉ ” የሚለው ቃል በማ
ገናዘብ እናስተውል ( ይሁዳ ፩፥ቁ፱
ራእይ ፲፪ ቁ ፯ ።) ስለዚህ ለኢያሱ
ተገልጾ የእግዚአብሔር ሠራዊት
አለቃ ሆኜ መጣሁ ያለው ራሱ እግ
ዚአብሔር ሳይሆን የእግዚአብሔር
መላእክት አለቃ ሚካኤል መኾኑን
አስተውለህ ቅሬታህን አስወግድ
ብለን በክርስቲያናዊ መንፈስ ስንመ
ክርህ በቅንነት እንደምትቀበለን ተስፋ
በማድረግ ነው ።

ከጠያቂው፡- ፬ “፪ኛ/ኢሳ ፵፱፥፳፫።
ነገሥታትም እቴጌዎቻቸውም ግን
ባራቸውን ዝቅ አድርገው ይሰ
ግዱልሻል የተባለች ጽዮንነች ።
ጽዮን ደግሞ (በዕብ ፲፪፥፳፪) የሕ
ያው እግዚአብሔር ከተማ የሆነችው
ሰማያዊት ኢየሩሳሌም ናት ። በሌላ
አጠራር መንግሥተ ሰማያት ለሆ
ነችው ጽዮን ተሰገደላት ይህም
ማለት የእግዚአብሔር መንግሥት
መመለኩን እንጂ ፍጥረታት እን
ደተሰገደላቸው አያመለክትም ።”
ብለሃል ።

ከአዘጋጆች ፡- ፬ “ይሰግዱልሻል ”
ተብሎ ትንቢት የተነገረላት “ጽዮን
ነች ማለትህ እውነት ነው ። በዚህ
አገባብ ጽዮን የተባለችው መንግ
ሥተ ሰማያት ነችን? መንግሥተ ሰማ
ያት የእግዚአብሔር መንግሥት ትባ
ላለች የተሰገደላትም ለእግዚአብ
ሔር መንግሥት እንጂ ለሌላ አይ
ደለም ብለህ የተረጐምከው ትክ
ክል አይደለም በዕብ ፲፪፥ቁ፳፪
የተጠቀሰላት ደብረ ጽዮን (የጽዮን
ተራራ ) መንግሥተ ሰማያት መኾኗን
እኛም ቢኾን እናምናለን ። በሌላ
አጠራር መንግሥተ ሰማያት የእ
ግዚአብሔር መንግሥት ተብላም
ትጠራለች ቅዋሜአችን በዚህ ላይ
አይደለም ያለ አገባቡ ስለተተረ
ጐመ ያንን ማስተካከል ይኖራል ።
ስለ ጽዮን መጽሐፍ ቅዱስ በልዩ
ልዩ ቦታ የተለያየ ትርጉም ይዞ
ይገኛል አንዳንድ ጊዜ ጽዮን በጎ

ብረት ጣምራ ትርጉም ይዛ ስት
ገኝ ሌላ ጊዜ ግን ለአንድ ነገር
ብቻ መግለጫ ሆና ትቀርባለች ።
ይኸንንም በዝርዝር እንመልከት ።

ሀ) “ ነገር ግን ዳዊት አምባይ
ቱን ጽዮንን ያዘ እርሷም የዳዊት
ከተማ ናት ዳዊትም በአምባይቱ
ውስጥ ተቀመጠ የዳዊትም ከተማ
ብሎ ጠራት ። ዳዊትም ዙሪያዋን
ከሚሎ ጀምሮ ወደ ውስጥ ቀጠራት
(፪ኛ ሳሙ ፭ ቁ ፯ና ፱ ።) ጠላቶ
ቹን ድል ያደረገበት ደብረ ጽዮን
(የጽዮን ተራራ ) ለዳዊት መናገሻ
ከተማው ናት የእግዚአብሔር
ታቦት መኖሪያ ሆናለች ። (፪ኛሳሙ
፮፥፲-፲፪ ) በዚህ አገባብ ጽዮን ከዳ
ዊት ከተማነት አልፋ ሌላ ጣምራ
ትርጉም የላትም ።

ለ) የእግዚአብሔር ቤተመቅደስ
የተሠራበት ሥፍራም የጽዮን ተራራ
ተብሎ ይጠራል ቤተመቅደስ እን
ደማለት ነው (ኢሳ ፰ቁ፲፰ ። ፲፰
ቁ፯፥፳፬ ቁ፳፫ )

ሐ) “. . . ድንግሊቱ የጽዮን ልጅ
ቀላል አድርጋሃለች በንቀትም ስቃ
ብሃለች የኢየሩሳሌም ልጅ በራ
ስህ ላይ ነቅንቃብሃለች ” (፪ነገሥ
፲፱፥ቁ ፳፩ ።)ሲል ስለ መላይቱ
ኢየሩሳሌም መናገሩ ነው ። በተጨ
መሪም መዝ ፵፯ ቁ ፪።፳፰ ቁ፴፭)
ተመልከት ።



www.ethiopianorthodox.org

# ስግደት ለማን ለምን?

ከለፈው የቀጠለ

፭/ በእውነትም አምላካችሁ . . . አለ እንጂ አምላካችን አላለም አምላኩን ለይቶ ከማያውቅ ሰው የሚደረግ ሥራ የእግዚአብሔር ፈቃድ አለበት ብሎ ማመን ስሕተት ነው “ ይኽ የጠያቂያችን ሰው የቅሬታ ነጥብ ነው ” የቅሬታውን መንሥኤ ንጉሡ ጣዖት አምላኪ ነበር አምላካችን አላለም አምላካችሁ ነው ያለው ፈጣሪውን የማያውቅሰው ነውና ድርጊቱን መቀበል ስሕተት ነው እናንተም ተሳስታችኋልና ማረም ይገባችኋል ለማለት የቀረበ ትችት ነው። በእኛ በኩል ከተሳሳትን ለመታረም ዝግጁ ነን ካልተሳሳትን ግን ተቺው ክፍል መታረም ግዴታው ነው ።

እንግዲህ በቅን ሕሊና በቅሉት ለብእና ሁነን ከዚህ በታች የተጻፉትን ጥቅሶች ከናቡከደነጾር አነጋገር ጋር እያመሳከርን እንመርምራቸውና ስሕተቱን እንፈልግ ።

፮/ “ ከኤልያስም የወደቀውን መጎናጸፊያ ወስዶ ውኃውን መታና የኤልያስ አምላክ እግዚአብሔር ወዴት ነው? አለ ። ውኃውንም በመታ ጊዜ ወዲህና ወዲያ ተከፈለ ኤልሳዕም ተሻገረ ኤልሳዕ አምላኬ በማለት ፈንታ የኤልያስ አምላክ ለምን አለ ለእርሱስ እግዚአብሔር አምላኩ አይደለምን? ወይስ ኤልሳዕን ጣዖት አምላኪ እንበለውን? ኤልሳዕ መምለኬ እግዚአብሔር ነው ጣዖት አምላኪ አይደለም አምላካችን በማለት ፈንታ ወይም አምላኬ በማለት ፈንታ የኤልያስ አምላክ ማለቱ በኤልያስ አባትነት ባለሟልነት አማላጅነት ማመኑን፣ በሌላ አባባል ኤልያስን ስለተሰጠው ጸጋ ማክበሩን ሲያመለክተን ነው። እንደዚሁም ናቡከደነጾር በዳንኤልና በሠለስቱ ደቂቅ አምላክ የተፈጸመውን ተአምራት ዐይቶ ከአመነ በኋላ የእነዳንኤልን ክብር ለመግለጽ አምላኬ ወይንም አምላካችን ሳይል አምላካችሁ ብሎ ባለሟልነታቸውን ለእግዚአብሔር ቀራቢዎች መኾናቸውን መገንዘቡን መስክሮላቸዋል ። ተገቢውን የጸጋ ክብር ሰጥቷቸዋል ። ለምነው ታዲያ በኋላ ጊዜ ቆይቶ ጣዖት አቁሞ ሠለስቱ ደቂቅን ወደ እቶነ እሳት ለምን አስጣላቸው? የሚል ሰው ቢኖር ይኽማ ስንኳን ከአሕዛብ ወገን የኾነ በተአምራት ያመነ ሰው ቀርቶ እግዚአብሔርን ሲያመልኩ የኖሩ ሰዎችም ተሳስተው ወደ አምልኮተ ጣዖት ተስበው እንደነበር ከመጽሐፍ ቅዱስ ብዙ መረጃ ማቅረብ ይቻላል ። ለምሳሌ የዳዊት ልጅ ሰሎሞን ያነገሠውን፣ሁለት ጊዜ ተገልጦ ያነጋገረውን የዳዊትን የአባቱን አምላክ ትቶ በአሕዛብ ሴቶች ፍቅር ተማርኮ ቤተ ጣዖት በመሥራቱ ፣ጣዖት በማምለኩ እግአዚብሔር እንደገሠፀው ተጽፎአል ። (፩ኛ ነገሥ ፲፩ ቁ፩ -፲፫) ሰሎሞን እንኳን ወደ አምልኮተ ጣዖት ከተሳበ ናቡከደነጾር ከአመነ በኋላ ወደ ጣዖት ተመለሰ ቢባል ብርቱ ድንቁ ምንድነው ሰሎሞን በንስሐ እንደተመለሰ ናቡከደነጾርም ተመልሷል። በእግዚአብሔር መንፈስ ተመርቶ የጻፋቸውን መጻሕፍት መጻሕፍተ ሰሎሞንን እነምሳሌን መክበብን የመሳሰሉትን ከመጽሐፍ ቅዱስ ደምረን ከተቀበልናቸው የናቡከደነጾርንስ የሃይማኖታዊ አነጋገር ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር አጣምረን የማንቀበልበት ምክንያት ምንድነው ? በውነቱ ስንመረምረው አንዳችም ምክንያት የለንም ።

፯/ “. . . አምላክህ ሕያው እግዚአብሔርን በማድጋ ካለው ከእፍኝ ዱቄት በማሰሮም ካለው ከጥቂት ዘይት በቀር እንጀራ የለኝም” ፩ኛ ነገሥ ፲፯ ቁ፰ -፲፮) የሰራጥታ ባልቴት በእግዚአብሔር እንጂ በጣዖት የምታመልክ ሰው አልነበረችም ። የሃይማኖት ስደተኛውን ነቢዩ ኤልያስን ለማስተናገድ የተመረጠችው ሴት ናት። የኤልያስ ፈጣሪ የእርሷም የሌሎችም ፈጣሪ መኾኑን ጠንቅቃ ታውቃለች እንዲህ ሆኖ ሳለ ስለምንድነው ኤልያስን አምላክህ ሕያው እግዚአብሔርን ያለችው ? ለምን አምላካችንን ሕያው እግዚአብሔርን ወይም አምላኬን ሕያው እግዚአብሔርን አላላችም? የኤልያስ አምላክ የፍጥረታት ኹሉ አምላክ ወይም የራሷም አምላክ መኾኑን ሳታምን ቀርታ ነውን? ይህችን የተመረጠች ሴት ከጣዖት አምላኪዎች እንመድባት ይሆንን? ጣዖት አምላኪ አይደለችም የሃይማኖትስ ስደተኛውን ነቢየ እግዚአብሔርን ለመቀበል በቅታለች ። እግዚአብሔር ባወቀ በረከተ ኤልያስን ሊያካፍላት በመውደዱ ለእግዚአብሔር ሰው ረድእ (አገልጋይ) አድርጎ መርጧታል ። እንግዲህ ይህች ሴት አምላክህ ሕያው እግዚአብሔርን ስላለች አምላካችን ወይም አምላኬ ሕያው እግዚአብሔርን ባለማለቷ ከጣዖት አምላኪዎች መመደብ እንደማይገባት ተረድተናል ።“በእውነት አምላካችሁ ” ስላለ ናቡከደነጾርን አምላኬ ወይም አምላካችን ለምን አላለም ብለን እንደ ጣዖት አምላኪ አድርገን ድርጊቱንም ሆነ አነጋገሩን የምንተችበት ምን ሰበብ አግኝተን ነው ። ናቡከደነጾር አምላካችሁ በማለቱ አይተችም የጸጋ ስግደት ማቅረቡም ትክክለኛ ነው ። በዚህ ሥራው ይመሰገን በታል እንጂ አይወቀስበትም ነቀፌታችንን ማረም ከስሕተታችን መመለስ ከተቺዎች የሚጠበቅብን መንፈሳዊ ግዴታችን መኾኑን ዕንወቅ እንረዳ ከስሕተታችን እንመለስ ።

፰/ “አብድዩም በመንገድ ሲሄድ እነሆ ኤልያስ ተገናኘው አብድዩም አወቀው በግንባሩም ተደፍቶ ጌታዬ ሆይ ኤልያስ አንተነህ አለ ኤልያስም ? እኔ ነኝ ሂደህ ለጌታህ ኤልያስ ተገኝቷል በል አለው ። አብድዮም አለ እኔ ባሪያህን እንዲገድል በአክዓብ እጅ አሳልፈህ ትሰጠኝ ዘንድ ምን

www.ethiopianorthodox.org

ኃጢአት አድርጌአለሁ ? አምላክህ ሕያው እግዚአብሔርን ጌታዬ ይፈልግህ ዘንድ ያልላከበት ሕዝብ ወይም መንግሥት የለም ። ሁሉም በዚህ የለም ባሉ ጊዜ አንተን እንዳላገኙ መንግሥቱንና ሕዝቡን አምሏቸው ነበር . . . ” (፩ኛ ነገሥ. ፲፰፡፯-፲፰) አብድዩ እግዚአብሔርን የሚፈራ የእግዚአብሔርን ሰዎች የሚያከብር የነቢያተ እግዚአብሔር ባለውለታ የኾነ ሰው ነው ። ናቡከደነጾር ዳንኤልን እንዳከበረው እሱም ነቢዩ ኤልያስን በቃልም በሥራም አክብሯል የጸጋ ስግደት አቅርቦለታል። አምላኬ ወይም አምላካችን ሕያው እግዚአብሔርን ማለት ሲችል ኤልያስን ለማክበር ስለፈለገ አምላክህ ሕያው እግዚአብሔርን ብሎታል። ኤልያስ የአምላክ ወዳጅ ባለሟል መኾኑን ለመግለጽ ፈልጎ ነው። የእግዚአብሔር ነቢይ ለፈጣሪው አምልኮት ቀናዒ የኾነው ኤልያስ አነጋገሩንም ድርጊቱንም አልተቃወመም ነገሩ የማይገባ ቢኾን ኑሮ ኤልያስ አብድዩን ይገሥፀው ነበር እንጂ በአምንታ አይቀበለውም ነበር። አልገሠፀውም ድርጊቱ ከፈቃደ እግዚአብሔር አለመውጣቱን ስለተረዳ ሊገሥፀው አልቃጣም ። ነቢዩ ዳንኤልም እንደ ኤልያስ ናቡከደነጾርን ሊገሥፀው ያልቃጣበት ምክንያት ቃሉም ሥራውም ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጭ ያልኾነ ድርጊት መኾኑን ስለተገነዘበ ነው ። እኛስ ከነቢያት የበለጠ ቀራቢዎች ኾነን ነው እግዚአብሔር ያልገሠፀውን ሰው ድርጊትና አነጋገር የምንተቸው? በበኩላችን አንተችም ተቺዎችንም ተው ተመከሩ ትችት አያዋጣችሁም እንላቸዋለን ።

፬/ “ እውነት አምላካችሁ የአማልክት አምላክ የነገሥታት ጌታ ምሥጢርም ገላጭ ነው።”(ዳን ምዕ ፪ ቁጥር ፵፯) ከዚህ በላይ የተጠቀሰውን ኃይለ ቃል የተናገረው ማነው? በጣዖት አምልኮት ጨለማ ውስጥ ተውጦ የነበረው ፣ እግዚአብሔር በነቢዩ ዳንኤል አድሮ የረቀቀውን ምሥጢር በተአምራቱ ገልጾ ስላስረዳው በዳንኤል ፈጣሪ ከአመነ በኋላ ናቡከደነጾር የተናገረው ጥቅስ ነው። በእነ ዳንኤል አምላክ ማመኑ በምን ይታወቃል ? ቢሉ በቃሉ በተናገረው ምሥክርነት ፣ በተግባሩ በፈጸመው ድርጊት ይታወቃል። የእነዳንኤልን አምላክ በእውነት አምላካችሁ ምሥጢር ገላጭ ነው ብሎ በልቡ ያመነውን እምነት በአፉ መስክሮ አረጋግጧል ። በዚህም አነጋገሩ የዳንኤልን ሃይማኖት ትምህርት መቀበሉን ያስረዳናል ። በዳንኤል ምዕ፪ቁ ፳፰ ላይ ነቢዩ “ ምሥጢር የሚገልጥ አምላክ በሰማይ ውስጥ አለ እርሱም በኋላኛው ዘመን የሚሆነውን ለንጉሡ ለናቡከደነጾር አስታውቆታል ” ብሎ እግዚአብሔር ምሥጢር ገላጭ መኾኑን አስተምሮት ነበርና ይህንን ትምህርት ማመኑን ሲመሰክር ንጉሡ በእውነት አምላካችሁ ምሥጢር ገላጭ ነው ብሎ አምኗል መስክሯልም ።

የአማልክት አምላክ የነገሥታት ጌታ ማለቱም ይኽ አምላክ የእነ ዳንኤል ፈጣሪ መኾኑን ዐውቆ ሕልሙና ትርጓሜው እንደተገለጸለት ይኽም ሃይማኖታዊ ጥበብ በእግዚአብሔር ተገልጾለት የተናገረው ኃይለ ቃል መኾኑን እናምናለን ። አባባሉም ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር የሚጣጣም የሚስማማ እንጂ የሚጣል አይደለም ። ተመሳሳይ የኾኑትን አንዳንድ ጥቅሶች እንመልከታቸውና ጥርጥራችንን እናስወግድ ።

ሀ/ “ እንግዲህ አምላካችሁ እግዚአብሔር የአማልክት አምላክ የጌቶችም ጌታ ታላቅ አምላክ ኃያልም የሚያስፈራም በፍርድ የማያዳላ መማለጃም የማይቀበል ነውና እናንተ የልባችሁን ሸለፈት ግረዙ ከእንግዲህ ወዲህም አንገተ ደንዳና አትሁኑ። ” (ዘዳግ ፲፥፲፯ -፲፰) የሙሴ አነጋገርና የናቡከደነጾር የእምነት ቃል ተመሳሳይ መኾኑን እንመልከት ። ለሙሴ የገለጸ አምላክ አምልኮቱን ለናቡከደነጾርም እንደገለጸለት እናስተውል ።

ለ/ “ የአማልክትን አምላክ አመስግኑ ምሕረቱ ለዘለዓለም ነውና የጌቶችን ጌታ አመስግኑ ምሕረቱ ለዘላለም ነውና ” መዝ (፻፴፭ ቁ፪-፫) የነቢዩ የዳዊት ቃልም ከናቡከደነጾር አነጋገር ጋር መጣጣሙን ተመልከቱ እንግዲህ የዳዊት አምላክ ነገረ ሃይማኖትን ለናቡከደነጾር ገለጸለት እንበል እንጂ አንንቀፍ ።

ሐ/ “ ያንም መገለጡን በራሱ ጊዜ ብፁዕና ብቻውን የሆነ ገዥ የነገሥታትን ንጉሥና የጌቶች ጌታ ያሳያል ” (፩ጢሞ ፮፥፲፭) በመንፈስ ቅዱስ ተቃኝቶ ሐዋርያው ጳውሎስ የተናገረውም ቃል ከንጉሡ አነጋገር ጋር አንድ እንደኾነ እንይ ።

መ/ “ እነዚህ በጉን ይወጋሉ ፣ በጉም ( ክርስቶስም) የጌታዎች ጌታና የነገሥታት ንጉሥ ስለሆነ እነርሱን ድል ይነሣል ።”

(ራዕይ ፲፯ ቁ፲፬ ራእይ ፲፱ ቁ. ፲፮)

ለወንጌላዊው ለቅዱስ ዮሐንስ የተከሰተው ምሥጢር ለናቡከደነጾር ተገልጾለት እንደነበር እንረዳለን ለዳንኤል የጸጋ ስግደት በመስገዱ የምንነቅፍበት ምክንያት ከምን መረጃ ተነሥተን ነው በኋላ ጊዜ ቆይቶ ወደ ጣዖት አምልኮት ተመልሶ የለምን ሲባልም በጣዖት አምልኮት ፀንቶ አልኖረም በንስሐ ተመልሷል ብለን እንመልሳለን ። ሐዋርያው ቶማስ ተጠራጥሮ መመለሱን ካመንን የናቡከደነጾርን ከጣዖት በንስሐ መመለስ የማንቀበልበት ምክንያት ስለሌለ ተቃውሚችንን መተው ነቀፋችንን ማረም ይኖርብናል ። (ዮሐ ፳ ቁ፡፳፬ - ፳፱ ዳን ፫ቁ ፳፰ -፴ ዳን ምዕ፬ በሙሉ እንመልከት )

ለ/ ከጠያቂው የጸጋ ስግደት እንደማይገባ ለመግለጽ ከቀረቡት የተቃውሞ ሐሳቦች ውስጥ ከላይ ከተገለጸው ሐተታ ጋር መገናዘብ ያለበት በመኾኑ እንደሚከተለው ቃል በቃል ለማስፈር ተገደናል ።

፩/ እንደ ጴጥሮስ ያሉ የእግዚአብሔር ባሪያዎች የክብርና ጸጋ ስግደትን አልተቀበሉም (የሐዋ/ሥራ ፲ ፡ ፳፭ -፳፮ )ጴጥሮስ የቆርኔሌዎስን ስግደት አልተቀበለም መርዶክዮስም ለሐማ አልሰገደም (አስቴር ፫ ፡፪ ፡ ፩።)

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በአንዳንድ ቦታ ለሰዎችና ለመላእክት ስግደት እንደተደረገ ብናገኝም የድንጋጤና የፍርሃት ወይም ባለማወቅ መሆኑን ልናስተውል ይገባል ። ለምሳሌ ፪ኛ ነገሥት ፬፡፴፯ ሞቶ የነበረው ልጅዋ ሕይወት ስለዘራ፤(ሐዋ.ሥራ ፲፯ ፡፳፱) ሰው ያልጠበቀውና ከአእምሮ በላይ የሆኑ የእግዚአብሔር ድንቅ ሥራዎች ከመቅጽበት ሲከናወኑ ሲያይ አእምሮው ላይ የሚወድቀውን ሸክም መቋቋም ሲሳነው በመርበትበት ደስታና ድንጋጤ ተደባልቀው ትክክል ያልሆነ ድርጊት ይፈጸማል ። ይህ ዓይነቱ ድርጊት በየአንዳንዳችን ገጠመኝና ተመክሮ ያለ መሆኑ አይካድም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ደግሞ በጎ በጐው ነገር ብቻ ተመርጦ የተጻፈ ሳይሆን ክፉም ደጉም እንደአፈጻጸሙ ሁሉንም የያዘ ስለሆነ ማስቢያ አእምሮ የተፈጠረለት ሰው መልካ



www.ethiopianorthodox.org

ሙንና ክፉውን መርምሮ የመለየት ኃላፊነት አለበት ተብሏል ።

፩/ ከአዘጋጆች "እንደ ጴጥሮስ ያሉ የእግዚአብሔር ባሪያዎች የክብርና ጸጋ ስግደትም አልተቀበሉም" (የሐዋ. ሥራ ፲/፳፭-፳፮) ተብሎ የቀረበው ሐሳብ ምሥጢሩን ካለማስተዋል የመነጨ ትችት ነው ። ነገሩን ለማስታዋል ከቁጥር ፩ እስከ ፳፫ መመልከት ይኖርብናል። የመቶ አለቃ ቆርኔሌዎስ ትውልዱ ከአሕዛብ ወገን ሆኖ ሳለ በስነፍጥረት ተመራምሮ በአእምሮ ጠባይዕ ዐውቆ ፈጣሪ መኖሩን ተገንዝቦ በጸሎት ትጠምዶ ምጽዋት እየመጸወተ የሚኖር እግዚአብሔርን የሚያመልክ ሰው ነበር ። ክዕለታት በአንድ ቀን ከቀኑ በ፱ ሰዓት በጸሎት ቆሞ ሳለ መልአከ እግዚአብሔር ይገለጽለታል ቆርኔሌዎስም በድንጋጤ ጌታ ሆይ ምንድነው ብሎ መልአኩን ይጠይቀዋል ። ያም መልአክ ጸሎቱና ምጽዋቱ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት አግኝቶ እንደዐረገለት ከገለጸለት በኋላ ስምዖን ጴጥሮስን ከአለበት ቦታ አስጠርቶ ከእርሱ የሚማረው ነገር እንዳለ አስረድቶ መልአኩ ይሰወራል ። ለታማኝ ጭፍሮቹ የተገለጸለትን ምሥጢር ከአጫወታቸው በኋላ ወደ ቅ/ ጴጥሮስ ዘንድ ይልካቸዋል ። የቆርኔሌዎስ መልእክተኞች በጉዞ ላይ እንዳሉ ከቀኑ በስድስት ሰዓት ቅ/ጴጥሮስ በቁርበት ፋቂው በስምዖን ቤት በተዘጋጀለት ሰገነት ላይ ወጥቶ ጸሎቱን ሲያደርስ ራእይ ሦስት ጊዜ ተገልለታል ። የራእዩ ትርጓሜ ሳይገባው ቀርቶ ሲያወጣ ሲያወርድ መንፈስ ቅዱስ የቆርኔሌዎስ መልእክተኞች ተልከው መምጣታቸውን ከአስታወቀው በኋላ ሳይጠራጠር ከእነርሱ ጋር እንዲሄድ ያዘዋል ። በዚህ ጊዜ የራእዩ ትርጓሜ አሕዛብን ሳይጸየፋቸው ወንጌልን እንዲያስተምራቸው መኾኑን ተገንዝቦ ተከትሏቸው ሲሄድ መቶ አለቃው ከቤተሰቦቹ ከዘመዶቹና ከቅርብ ወዳጆቹ ጋር ሆኖ ሲጠባበቅ ነበርና ቅዱስ ጴጥሮስ ወደ ቤት ሲገባ ከእግሩ በታች ወድቆ ሰገደለት ። ወዲያው ቅዱስ ጴጥሮስ ተነሣ እኔ ራሴ ደግሞ ሰው ነኝ ብሎ አስነሣው ። ቀጥሎም ከእርሱም ጋር እየተነጋገረ ገባ ብዙዎችም ተከማችተው አግኝቶ "አይሁዳዊ ሰው ከሌላ ወገን ጋር ይተባበር ወይም ይቀርብ ዘንድ እንዳልተፈቀደ እናንተ ታውቃላችሁ ። ለእኔ ግን እግዚአብሔር ማንንም ሰው ርኩስና የሚያስጸይፍ ነው እንዳልል አሳየኝ ። ስለዚህም ደግሞ ብትጠሩኝ ሳልከራከር መጣሁ አሁንም በምን ምክንያት አስመጣችሁኝ ብዬ እጠይቃችኋለሁ አላቸው ።" ይላል ቅዱስ ጴጥሮስ እኔ ሰው ነኝ ማለቱ የትህትና አነጋገር ነው። ቆርንሌዎስ ለቅ/ጴጥሮስ የጸጋ ስግ. ት ሲሰግድለትም ቆርኒሎዎስም በእግዚአብሔር ፊት የከበረ ሰው መኾኑን ስላወቀ የቆርኒሌዎስን ክብር ለመግለጽ ሰው ነኝ በሚል አገላለጽ በትሕትና ሐዋርያው አክብሮታል። ይኸም የትሕትና ባሕል እንግዳ ከውጭ ሲመጣ ከቋሚ ላይ ወድቆ መስገድ ወይም ከተቀመጡበት ተነሥቶ እጅ ነሥቶ ኖር ማለት ። የተለመደ የትሕትና ስርዓት ነው እንግዳውም አይገባም በአግዜር በቅዱሳን ይላል ከዚህ የተለየ ሥርዓት አልተፈጸመም ቆርኔሌዎስ ለቅ/ጴጥሮስ የእግዚአብሔር ሰው መኾኑን ዐውቆ ቢሰግድለት ቅ/ጴጥሮስም አይገባኝም እኔ ሰው ነኝ ብሎ ለቆርኔሌዎስ ከበሬታ ቢሰጥ ትሕትናውን ቢገልጽ የጸጋ ሲጊድ ወይም የአክብሮት ስግደት እንደተቃወመ አድርጎ መጻፍ ከአለማስተዋል የመነጨ ነው ።

እሺ ቅ/ጴጥሮስ የእግዚአብሔር ባርያ ስለኾነ ቆርኔሌዎስ ያቀረበለትን ስግደት ሰው ነኝ በሚል አነጋገር ተቃወመ ብለን እንቀበል ። ሎጥ የእግዚአብሔር ባርያ የጽድቅ ሰው መኾኑ በራሱ በቅዱስ ጴጥሮስ እንደበት ተመስክሮለታል "ጻድቅ ሎጥም በመካከላቸው ሲኖር እያየና እየሰማ ዕለት ዕለት በዓመፀኛ ሥራቸው ጻድቅ ነፍሱን አስጨንቆ ነበርና በዓመፀኞች ሴሰኛ ኑሮ የተገፋውን ያን ጻድቅ ካዳነ ጌታ እግዚአብሔርን የሚያመልኩትን ከፈተና እንዴት እንዲያድን በደለኞችንም ይልቁንም በርኩስ ምኞት የሥጋን ፍትወት እየተከተሉ የሚመለለሱትን ጌትነትንም የሚንቁትን እየቀጣቸው ለፍርድ ቀን እንዴት እንዲጠብቅ ያውቃል ።" (፪ኛ ጴጥ. ፪፡፯-፲) መላእከት በእንግድነት መልክ ወደ ቤቱ ሲመጡ ጌቶቼ እያለ የጸጋ ስግደት ለምን አቀረበላቸው? የእግዚአብሔር ባሪያ ባይኾን ነውን ሎጥ ሲሰግድላቸው ጌቶቼ እያለ ሲያከብራቸው ለምን አትስገድልንም አላሉትም ? የእግዚአብሔር አገልጋዮች ባይኾኑ ነውን? መላእክቱን ምናልባት አብና ወልድ እንዳታደርጋቸው መጽሐፉ መላእክት መኾናቸውን ቁልጭ አድርጎ ገልጾታል (ዘፍጥ ፲፱፡፩-፫ ዕብ ፲፫፣፩-፪) ሎጥም ኾነ ቆርኒሌዎስ ያቀረቡት ስግደት የጸጋ ስለኾነ በእነርሱና በተከታዮቻቸው ላይ በኦሪት ዘፀአት ምዕ ፳፡፩-፮ የተጠቀሰውን ትእዛዝ እንደተላለፉ ተደርጎ ሊወቀሱ አይገባም ። ይልቁንስ የእግዚአብሔር ጸጋ የሚገኘው እንደ ሎጥና እንደ ቆርኒሌዎስ ክብር ለሚገባቸው ክብር በመስጠት ትሑት በመኾን ነው ። ትዕቢት ሰውን ይጐዳል ትሕትና ግን ክብርን ጸጋን ያሳጣል ለዚህም ምስክር የሚኾኑ የቅዱሳት መጻሕፍት ጥቅሶች እንመልከት ።

፩/ "ሰው ሳይወድቅ በፊት ልቡ ከፍ ከፍ ይላል ትሕትናም ክብራትን ትቀድማለች ።"(ምሳሌ ፲፰ ቁ ፲፪)

፪/ "እንዲሁም ጎበዞች ሆይ ለሽማግሌዎች ተገዙ ሁላችሁም እርስ በርሳችሁ እየተዋረዳችሁ ትሕትናን እንደ ልብስ ታጠቁ እግዚአብሔር ተዕቢተኞችን ይቃወማልና ለትሑታን ግን ጸጋን ይሰጣል ።"(፩ኛ ጴጥ ፭ ቁ፭)

፫/ "አቤቱ በድንኳንህ ውስጥ ማን ያድራል? በተቀደሰውም ተራራህ ማን ይኖራል?እግዚአብሔርንም የሚፈሩትን የሚያከብር እንዲህ የሚያደርግ ለዘላለም አይታወክም" (መዝ ፲፬ - ፲፭ቁ፩ ፬ና ፭)

፬/ "ነቢይን በነቢይ ስም የሚቀበል የነቢይን ዋጋ ይወስዳል ጻድቅንም በጻድቅ ስም የሚቀበል የጻድቁን ዋጋ ይወስዳል" (ማቴ ፲ ቁ ፵፩) (፪ ነገሥ ፪ ቁ፯-፲፭)

በኤልያስ ያደረ የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ ለኤልሳዕ ዕጥፍ ድርብ ሆኖ እንደተሰጠው በመረዳታቸው የነቢያት ልጆች የጸጋ ክብር ሰጥተውታል "በፊቱ ወድቀው ተደፉ" ይላል የጸጋ ስግደት አቀረቡለት ማለት አይደለምን? ኤልሳዕም በመቀበሉ እንተቸው ይሆን? እሱን ለመተቸት እረ ለመኾኑ እኛ ማነን? ዐቅማችን ደረጃችንን ማወቅ ይገባናል ።

የነቢያት ልጆችም በፊቱ በመደፋታቸው መምለኪያን ጣዖታት አያሰኛቸውም ። ኤልሳዕም ዝም ብሎ



www.ethiopianorthodox.org

በመቀበሉ አልተሳሳተም ። እንደ ጣያ ትም አይቆጠርም ። ቅ/ጴጥሮስን የእግዚአብሔር ባሪያ ስለኾነ የጸጋ ስግደትን ተቃወመ ካልኽ ኤልሳዕን ዝም ብሎ የጸጋ ስግደትን በመቀበሉ ምን ትለው ይሆን፣ ደቂቀ ነቢያትስ የጸጋ ስግደት ስላቀረቡለት ተሳሳቱ ፣ ኤልሳዕም ተሳስቷል፣ ነቢያቱም ተሳስተዋል የምትል ከኾነ የእኛ መልስ የተሳሳትከው አንተ ስለኾንኽ ታረም ንስሐ ግባ የሚል ይሆናል ።

እኛስ ኤልሳዕንም ሆነ ነቢያቱን ተሳስተዋል አንልም። የታነጽነው በሐዋርያትና በነቢያት መሠረት ላይ ስለኾነ እንኳን የኛ ብጤ ሰው መልአክ ነኝ ብሎ የአልኾነ ትምህርት ቢያመጣ አንቀበለውም ። (ኤፌ ፪ ቁ ፳ ገላ ፩፡፰)

ለሰዎችና ለመላእክት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስግደት እንደ ቀረበላቸው ከአመንክ በኋላ ያመን ከውን ሳትንደው ይኸ የተደረገው በድንጋጤ በፍርሃት ወይም ባለማወቅ ነው ብለሃል ።

ለዚህም መረጃ ፪ኛ ነገሥ. ፬፡፴፯ና የሐዋ ሥራ ፲፡፳፱ ጠቅሰሃል እውን መረጃው አንተ እንዳልኸው ይሆን

፪ኛ ነገሥ. ምዕ ፬ ከቁጥር ፲፰-፴፯ ያለውን ታሪኩን ስንመለከት ልጅዋ በድንገት ታሞ የሞተባት ሱነማዊት በኤልሳዕ ጸሎት አማላጅነት እግዚአብሔር እንደሚያስነሳላት በማመን ወደ ኤልሳዕ ከሄደች በኋላ ስታገኘው የጸጋ ጌትነት (ክብር) ያለው መኾኑን በመግለጽ ከዚያ በፊትም በጸሎቱ ልጅ ማግኘቷን በማስታወስ ችግሯን አዋየችው በቁጥር ፳፰ "በውኑ ከጌታዬ ልጅን ለመንሁ እኔም አታታልለኝ አላልሁምን አለች" ይላል ኤልሳዕ የጸጋ ጌትነት ያለው በጸሎቱ (በምልጃው) ከፈጣሪው ለምና ልጅ እንዳሰጣት ያላትን እምነት የሚገልጽ አነጋገር ነው ። ምንም እንኳን ኤልሳዕ የእጁን በትር ላግልጋዩ ለግያዝ ሰጥቶ ልጅን እንዲያስነሳለት ቢልክ ውም ሱነማዊት ግን የኤልሳዕን መንፈሳዊ ደረጃ በውል ስለምታውቅ እንዲለያትና እንዲቀር አልፈቀደችም እንዲህ ብላ ተማጸነችው የሕፃኑም እናት "ሕያው እግዚአብሔርን በሕያው ነፍስህም እምላለሁ አልተውህም" አለች። (ቁ፴) በዚህም ምክንያት ነቢዩ ተነሥቶ ተከትሏት ወደ ቤቷ ደረሰ ያች ሴት እንዳሰበችው ግያዝ ሕፃኑን ሊያሥነሳው ደረጃው አልፈቀደለትም ። ከቁጥር ፴፰-፴፮ እንደተገለፀው ኤልሳዕ መላልሶ ከጸለየ በኋላ ሕፃኑ ሊነሣላት ችሏል። ለእናቱ ሕፃኑን በሕይወት ሲሰጣት ቀድሞውኑ ኤልሳዕ የጸጋ ጌትነት እንዳለው ስለምታውቅ የጸጋ ክብር በደስታ በፍጹም ትሕትና አቅርባለታለች ።

ቁጥር ፴፯ ላይ "ገብታም በእግሩ አጠገብ ወደቀች በምድርም ላይ ተደፋች ልጅዋንም አንሥታ ወጣች" ይላል ደነገጠች ፈራችና ባለማወቅ የጸጋ ስግደት አቀረበችለት የሚል ቃል አልተጻፈም ። በመደሰት ፊንታ የምትፈራበትና የምትደነግጥበት ምክንያት ምንድነው፣ ባለማወቅ ሰገደችለት እንዳይባል የኤልሳዕን ክብርና የእግዚአብሔር ባለሟልነት ሲጀመር ጀምሮ ከመሠረቱ ታውቀዋለች ። እሷን በድንጋጤ በፍርሃት ወይም ባለማወቅ ሰገደችለት ብንል የእግዚአብሔር መንፈስ ዕጥፍ ሆኖ የተሰጠው ኤልሳዕ የእግዚአብሔር ባርያ ሆኖ ሳለ ለምን ስሕተቷን ሳያርምላት በዝምታ አለፈው፣ ቅዱስ ጴጥሮስ እንደተናገረው እኔ ሰው ነኝ ተነሺ ለምን አላላትም? ሱነማዊቱ የጸጋ ስግደት በማቅረቧ ኤልሳዕም ዝም ብሎ በመቀበሉ ሁለቱም አልተሳሳቱም ። በቅዱስ ጴጥሮስ ንግግርና በኤልሳዕ ዝምታ መካከል የሁኔታ ልዩነት እንጂ የምሥጢር ልዩነት አይታይም ። ሁለቱም ተገቢውን የመንፈሳዊ አባታቸውን ተግባር ፈጽመዋል ቆርኔሌዎስም ሱነማዊቱም የፈጸሙት የትሕትና ሥራ ባለማወቅ በድንጋጤና በፍርሃት አይተረጎምም ።

በሐዋ ሥራ ምዕ ፲ ቁ.፳፱-፴ የተፈጸመውም ድርጊት ከላይኛው አባባል ጋር የሚስማማ እንጂ የሚጣላ አይደለም ። ታሪኩን ከቁጥር ፲፱ እስከ ፴፬ መመልከት ነው ።

የወኅኒው ጠባቂ ቅ/ጳውሎስን ሲላስን ተጠንቅቆ እንዲጠብቃቸው እንዳያመልጡ ስለታዘዘ ግዳጁን ለመወጣት እግራቸውን በግንድ አጣብቆ ጠርንቆ ከአሠራቸው በኋላ ወደ ውስጠኛው የወኅኒ ክፍል ጣላቸው መንፈቀ ሌሊት ሲሆን ጳውሎስና ሲላስ እየጸለዩ በዜማ እግዚአብሔርን ሲያመሰግኑ እስረኞች ሁሉ ሲያዳምጧቸው ነበር ። በተአምራት የመሬት መናወጥ ተደረገና የወኅኒው ደጆች ተከፋፈቱ የእስረኞችም እስራት ተፈታ ።

በዚህን ጊዜ የወኅኒው ጠባቂ ከእንቅልፉ ነቅቶ ቢመለከት ደጆቹ ተከፍተው አየ እስረኞቹ ሁሉ ያመለጡ መስሎት ራሱን በሰይፍ ሊያጠፋ በተዘጋጀ ጊዜ ቅዱስ ጳውሎስ ድምፁን ከፍ አድርጎ እንዲህ አለው "ሁላችን በዚህ አለንና በራስህ ክፉ ነገር አታድርግ" የወህኒ ጠባቂውም ከድንጋጤውና ከፍርሃቱ ተመልሶ የተደረገው ተአምራት አስደንቆት እነ ጳውሎስየእግዚአብሔር ባለሟሎች መኾናቸውን በመገንዘብ ጨለማ ነበርና መብራት ለምኖ ወደ ውስጥ ከገባ በኋላ እየተንቀጠቀጠ ከጳውሎስና ከሲላስ ፊት ተደፋ ። የጸጋ ስግደት አቀረበላቸው ፍርሃቱም መንቀጥቀጡም የእግዚአብሔርን ኃያልነት የእነ ጳውሎስን ቅድስና ከማወቅ ከማድነቅ የተነሣ የተፈጸመ ነው እንጂ ሌላ ምክንያት የለውም። ይኸም ሁኔታ ስንኳን ለሃይማኖት እንግዳ በኾነው ከአረማውያን ወገን ለሚኾን የወኅኒ ጠባቂ ላይ ብቻ የሚከሰት ሳይሆን የእግዚአብሔር ጠባቂዎች በሆኑት ቅዱሳን ሰዎችም ላይ የሚታይ ጠባይ ነው ። ደግ ሥራ ባይኖራቸውም አጋንንት እንኳን በበኩላቸው በእግዚአብሔር ፊት ይንቀጠቀጣሉ ይፈራሉ ፍርሃታቸው ከቅዱሳን ፍርሃት የተለየ ቢኾንም አምልኮታቸውን ሲገልጹ በመፍራት በመንቀጥቀጥ እንደኾነ ሐዋርያዋ ያዕቆብ ይነግረናል "እግዚአብሔር አንድ እንደሆነ አንተ ታምናለህ መልካም ታደርጋለህ አጋንንት ደግሞ ያምናሉ ይንቀጠቀጡማል።"(ያዕ፪፡፲፱) ይኸ ሰውም የተንቀጠቀጠው የእግዚአብሔር ድንቅ ሥራ በሐዋርያቱ ላይ ስለተገለጸ እግዚአብሔርን በመፍራት ቅዱሳንን በማክበር የተደ



www.ethiopianorthodox.org

ረገ ነው ። ሰይጣን እንኳን የሐሰት አባት ሆኖ ሳለ የቅዱሳንን ክብር ዐውቆ ይፈራል። (የሐዋ ሥራ ፲፱፡ ፲፭-፲፯) ነቢዩ ዳዊትም "እግዚአብሔር በቅዱሳኑ ላይ ድንቅ ነው" (መዝ ፷፯ ቁ ፴፭) ማለቱ ስለዚህ ነው ።

አእምሮ ላለው ሰው መንፈስ ቅዱስ ለቀረበውማ ሰው እንኳን ቅዱሳን ሰዎችና መላእክት እግዚአብሔር በረድኤት የሚገለጽበት ሥፍራ እንኳን የከበረ ነው። ቦታው እንደማንኛውም ሥፍራ አይታይም ይፈራል ይከበራል ።

በሎዛ ሳለ ያዕቆብ ሌሊት እግዚአብሔር በራእይ ስለተነጋገረው ማለዳ ተነሥቶ የተናገራቸው ኃይለ ቃላት ከማስረጃችን ጋር ይገናዘባል ። " ያዕቆብም ከእንቅልፉ ተነሥቶ በእውነት እግዚአብሔር በዚህ ስፍራ ነው እኔ አላወቅሁም ነበር አለ ፈራ እንዲህም አለ ። ይህ ስፍራ እንዴት ያስፈራ? ይህ ስፍራ የእግዚአብሔር ቤት ነው እንጂ ሌላ አይደለም ይህም የሰማይ ደጅ ነው።" (ዘፍጥ ፳፰ቁ ፲፮-፲፯) እግዚአብሔር የተገለጸበት ስፍራ ካስፈራ ካንቀጠቀጠ ቅዱሳንማ ምን ያሕል ያንቀጠቅጡ ፣ ያስፈሩ ይሆን ? ብሎ ከመዳፈር ከማቃለል በመቆጠብ ፈንታ የጸጋ ስግደትን ሲቀርብላቸው አይገባም ብሎ መፋለም መጽሐፍ ቅዱስን ተመልክቻለሁ ከሚል ሰው ቀርቶ ከተራ ሰው አይጠበቅም። የወኅኒ ጠባቂው ሰው መንቀጥቀጥ ምሥጢሩ ይኸ ሲኾን ይኸንኑ አባባል ለማጎላመስ ሰውየውያ ደረገውን ድርጊት ስንመለከት ምን ያህል የጸጋ አክብሮት ለሐዋርያቱ እንደሰጣቸው መረዳት እንችላለን ። በጳውሎስና በሲላስ ፊት ተደፍቶ የጸጋ ስጊድ ካቀረበላቸው በኋላ ከወኅኒ ውስጥ ወደ ውጭ አውጥቶ " ጌቶቼ ሆይ እድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል ብሎ ጠየቃቸው እነርሱም በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተና ቤተሰቦችህም ትድናላችሁ አሉት በዚያች ሌሊት ከነቤተሰቡ አምኖ በመጠመቅ ሐሤት አድርጓል ።"

በፊታቸው ተደፍቶ ሲሰግድላቸው ጌቶቼ እያለ ሲያከብራቸው ቅ/ ውሎስና ሲላስ እንደ ቅዱስ ጴጥሮስ የእግዚአብሔር ባርያዎች ሳይኾኑ ቀርተው ነው አትስገድልን ጌቶችም አትበለን እኛ እኮ ሰዎች ነን ሳይሉ በዝምታ ያለፉት? ባለማወቅ ይሆናል ፈርቶ ደንግጦ ስለሆነ ግዴለም እንለፈው ብለው ይሆን? ቅዱስ ጳውሎስን ያሕል ሐዋርያ ስሕተትን ሳያርም በይሉኝታ ወይም በቸልተኝነት እንደማያልፍ ዜና ሕይወቱ ያስረዳናል

በድንጋጤም ይሁን ባለማወቅ የተሳሳቱ ካሉም ከመምከርና ወዲያውኑ ከማረም የማይመለስ ሐዋርያ መኾኑን በይበልጥ ለመረዳት ከፈለግን በሐዋ ሥራ ምዕ ፲፬ ከቁጥር፰ ፲፰ የተጻፈውን አንብበን ቅዱስ ጳውሎስ አረማውያንን ከስሕተት እንዴት እንደመለሳቸው እንይ" እናንተ ሰዎች ይህን ስለምን ታደርጋላችሁ እኛ ደግሞ እንደ እናንተ የምንስማ ሰዎች ነን ። ከዚህም ከንቱ ነገር ሰማይንና ምድርን ባሕርንም በእነርሱም ያለውን ሁሉ ወደ ፈጠረ ወደ ሕያው እግዚአብሔር ዘወር እንድትሉ ወንጌልን እንሰብካለን " (የሐዋ ሥራ ፲፬ ቁ ፲፭) በማለት 'ሕዝቡን በጭንቀት አስተውአቸው።") (ም ፲፬ ቁ ፲፰) ይላል ለእግዚአብሔር የሚሰጠው የአምልኮት ስግደት ወይም መሥዋዕት በሚቀርብላቸው ጊዜ ወዲያውኑ የዕርምት እርምጃ ወሰዱ እንጂ ፈርተው ደንግጠው ወይም ባለማወቃቸው ይሆናል በማለት በዝምታ ያለፉበት ጊዜ የለም ። የወኅኒ ጠባቂው ያቀረበው ስግደት የአክብሮት መኾኑን ስለተገነዘቡ ወደ ክርስትና ሃይማኖት መሩት እንጂ በልስጥራን የነበሩትን ሕዝቦች እንዳረሟቸው አላረሙትም ተባስተሃል የማይገባ ተግባር ፈጽመሃል አላሉትም "መርዶክዮስም ለሐማ አልሰገደም አስቴ ፫፡፪-፬ ብሎ ጠያቂያችን ለቅዱሳን የጸጋ ስግደት እንደማያስፈልጋቸው ለማስረጃነት ጠቅሷል ። ቅዱሳንን እንደ ሐማ ቆጥሯቸዋል ማለት ነው ። የመርዶክዮስ አለመስገድ በአርያነት ተወስዶ ለቅዱሳን ምንም ዓይነት የጸጋ ስግደት እንዳናቀርብ ለማስገንዘብ የቀረበ ጥቅስ ሆኖ አግኝተነዋል ።

መርደክዮስ ለሐማ ያልሰገደበት ምክንያት ለምን እንደሆነ በቅድሚያ መርምሮ መረዳት ሳያውቁ ሳይጠነቀቁ ሌሎችን ከመንቀፍ ያድናል ። ሐማ በንጉሡ በአርጤክስስ የተሾመ ሰው ነበር ።

ለሐማ ሰዎች እንዲሰግዱለት ትእዛዝ ያስተላለፈው ንጉሡ ነው ንጉሡም ሆነ ሐማ የአይሁድ ወገኖች አይደሉም ። በእግዚአብሔር የሚያመልኩ እንደ መርዶክዮስ ያሉትን አይሁዶች ማርከው በቅኝ ግዛት ይገዟቸው ነበር ። የአይሁድ ሕዝብ ጠላቶች ናቸው በሌላም በኩል ጣዖት ከሚያመልኩ ከአሕዛብ ወገን ናቸው ። በእግዚአብሔር የሚያመልኩ አይደሉም ። መጽሐፈ አስቴርን ከምዕ ፩ እስከ ምዕ ፯ ከቁ፩-፲ ድረስ ብንመለከት ሐማ ምን አይነት ክፉና ትዕቢተኛ ተንኮለኛ ሰው መኾኑን እንመለከታለን ። ንጉሡም ሆነ ሐማ ከአሕዛብ ወገን ስለኾኑ የአሕዛብን የአምልኮት ሥርዓት መፈጸማቸው የታወቀ ነው ። የአሕዛብ ነገሥታት አማልክት ነን እያሉ ከነመኳንንቶቻቸው እንደሚመለኩ ታሪካቸው ይነግረናል ። የሐማ ጠባይና የሄሮድስ ባሕርይ ተመሳሳይ ነው እንደ እግዚአብሔር መመለክ ይፈልጋሉ ። መጨረሻቸው ግን አላማረም ሁለቱም በትዕቢታቸው በክፋታቸው ተቀሥፈዋል ። (የሐዋ ሥራ ፲፪ቁ ፳-፳፫)

መርዶክዮስ ለሐማ እንኳን የአምልኮት የጸጋም ስግደት አለማቅረቡ ተገቢ ነው ። እኛም ብንኾን ለጣዖት አምላኪው ለሐማና ለመሰሎቹ የጸጋ ስግደት ይቀርብላቸዋል እንልም ማንም ሹም ነኝ ባይ መጥቶ ወይ እንደ ፈጣሪ አድርጋችሁ ስገዱልኝ ወይም እንደ ቅዱሳን ሰዎችና መላእክት አድርጋችሁ የጸጋ ስግደት አቅርቡልኝ ቢል እንኳን የአምልኮት ስግደት ለፈጣሪ ብቻ የምናቀርበውን ለማንም ፍጡር የማንሰጠውን ክብር ልናቀርብለት ይቅርና ተገቢ የሆነውን አነስተኛውን የጸጋ ክብር እንኳን አናቀርብለትም መልሳችን የሚኾነው መድኃኒታ



www.ethiopianorthodox.org

ችን እንዳስተማረን ሂድ አንተ ሰይጣን ለጌታህ ለአምላክህ ስገድ እርሱንም ብቻ አምልክ ተብሎ ተጽፎአልና (ማቴ ፬ ቁ ፲) የሚል ነው ።

ለሐማ መርዶክዮስ የሚሰግድበት ምክንያቱም ምንድነው? ሐማ አምላክ ነውን ወይስ ከቅዱሳን አንዱ ነውን? ለጣዖት አምላኪ ሰው ያውም እንደ አምላክ ለመመለክ ለሚፈልግ ትእቢተኛ ሰው እንዴት ይስገድለታል? እንደ እነዚህማ ላሉ ሰዎች መስገድ የእግዚአብሔርን ቃል መተላለፍ ስለኾነ ያስቀጣል ጸጋን የሚያስገኝ ሳይኾን ከጸጋ የሚያርቅተግብር በመኾኑ እኛም እንደ መርዶክዮስ ለሐማና ራሳቸውን ለሚያኮሩ ተዕቢተኞች በምንም ዓይነት ቢሆን የጸጋ ስግደት ይገባቸዋል አንልም ።

(ዘጸአ ፳፫፡፫-፯ ዘጸአ ፴፬፡፲፬-፲፭) በመጽሐፍ ቅዱስ ከጥንት ጀምሮ ስግደት ያለ መኾኑን ለመረዳት አንዳንድ ጥቅሶች በተጨማሪ ተመልክተን ለማስተዋል እንሞክር ።

ሀ፡ ዘፍጥ ፴፫ ፣ ፩-፯ "ያዕቆብ ወደ ወንድሙ እስኪደርስ ድረስ ወደ ምድር ሰባት ጊዜ ሰገደ "ሴቶች ባሪያዎችም ከልጆቻቸው ጋር ቀርበው ሰገዱ ደግሞም ልያና ልጆችዋ ቀርበው ሰገዱ ከዚያም በኋላ ዮሴፍና ራሔል ቀርበው ሰገዱ" ይላል ።

ያዕቆብ ከነቤተሰቦዎቹ ለዔሳው መስገዳቸው ዔሳውን ማምለካቸው አልነበረም ታናሽ ታላቅን ማክበር የትሕትና ሥርዓት በመኾኑ ሃይማኖታዊ ያዕቆብ ለታላቅ ወንድሙ ከበሬታን አሳይቷል ። ዔሳው ያዕቆብን እነዚህ ምኖችህ ናቸው ብሎ በጠየቀውም ጊዜ እግዚአብሔር ለባርያህ የሰጠኝ ልጆች ናቸው ብሎታል ። እግዚአብሔርን የሚያመልክ ሆኖ ሳለ ለታላቅ ወንድሙ መስገዱ ባርያህ ነኝ ማለቱ የያዕቆብን ትህትናውን ያሳያል የትሕትና ሥራና አነጋገር ካልኾነ ያዕቆብ የገዛ ወንድሙን እንዴት ባርያህ በማለት በራሱ ላይ ጌታ ያደርገዋል ለምንስ ይሰግድለታል?

ያዕቆብ እግዚአብሔርን ባያውቅ እምነት ባይኖረው ነውን? አይደለም የያዕቆብማ ሃይማኖት በብሉይም በሐዲስም የተመሰከረለት የጠራ እንከን የሌለበት መኾኑ ታውቋል ኤልያስ እንኳን በጸለየ ጊዜ የያዕቆብ (የእስራኤልን) ሃይማኖታዊ ክብር ገልጿል ። ቅዱስ ጳውሎስም የእምነቱን ጥንካሬ መስክሮለታል ። (፩ኛ ነገሥ ፲፰ ቁ ፴፮ ዕብ ፲፩ ቁ.፳፩) በእድሜ ታናሽ የኾኑ በዕድሜ የሚበልጣቸውን እንዲያከብሯቸው እግዚአብሔር አዝዟል "በሽበታሙ ፊት ተነሣ ሽማግሌውንም አክብር አምላክህንም ፍራ እኔ እግዚአብሔር ነኝ" ዘሌዋ ፲፱ ቁጥር ፴፪) "ጎበዞች ሆይ ለሽማግሌዎች ተገዙ ሁላችሁም እርስ በርሳችሁ እየተዋደዳችሁ ትሕትናን እንደ ልብስ ታጠቁ" ( ፩ጴጥ ፭ ቁ፭) እሊህ ሁለት ጥቅሶች ታናሽ ታላቅን እንዲያከብር ያስረዳሉ ያዕቆብም ለዔሳው መስገዱ ታናሽ ታላቅን ማክበር እንደሚገባ በሕገ ልቡና በአእምሮ ጠባይዕ በማወቁ ነው ።

ለ/ ዘጸአ ፲፰ ፡፮ -፯ " ሙሴንም እኔ አማትህ ዮቶር ሚስትህም ከእርሷም ጋር ሁለቱ ልጆች መጥተንልሃል አለው ። ሙሴም አማቱን ሊገናኝ ወጣ ሰገደም ሳመውም እርስ በርሳቸውም ደኅንነታቸውን ተጠያየቁ ወደ ድንኳንም ገቡ " ሙሴ ለአማቱ መስገዱ ማምለኩ ሳይኾን ማክበሩ ነበር ታናሽ ታላቅን ልጅ አባትን ማክበር ይገባል ። ቅዱሳንንም የምናከብራቸው በፍጹምነታቸው ከእኛ በላይ ስለኾኑ ነው ። ለምሳሌ የጥንት ክርስቲያኖች ሐዋርያትን የሚያከብሯቸው የሐዋርያትን ፍጹምነት በመረዳታቸው ነበር ፣ (የሐዋ ሥራ ፭ ቁ፲፪ -፲፮) በማክበራቸውም ተጠቀሙበት እንጂ አልተጎዱበትም እኛም ቅዱሳንን ብናከብራቸው እንጠቀማለን እንጂ እንጎዳም ።

ሐ/ ዘፍጥ ፵፰ ፡፲፩ -፲፪ " እስራኤልም ዮሴፍን ፊትህን አያለሁ ብዬ አላሰብሁም ነበር እነሆም እግዚአብሔር ዘርህን ደግሞ አሳየኝ አለው ። ዮሴፍም ከጉልበቱ ፈቀቅ አደረጋቸው ወደ ምድርም በግምባሩ ሰገደ።" ለአባቱ የጸጋ ስግደት በማቅረቡ ተሳሳተ አይባልም በእርእያነት ተጠቅመን የሥጋ ብቻ ሳይኾን የሃይማኖት አባቶቻችንን ነቢያትን ሐዋርያትን ጻድቃንን ሰማእታትን እናከብራቸዋለን የጸጋ ስግደትም እናቀርብላቸዋለን ። (ዕብ ፲፫ ቁ፯ ኤፌ ፮ቁ፩)

መ/ ፩ሳሙ ፳፰ ቁ.፲፬ " ሳኦልም እንደሆነ አወቀ በፊቱም ተጎንበስ በምድርም ላይ እጅ ነሣ " ይላል ሳኦል በሌላውም ኃጢአቱ ሲወቀስ ለሳሙኤል በመስገዱ አልተወቀሰበትም ። ናቡከደነጾር ዳንኤልን እንዳከበረ ሳኦልም ሳሙኤልን አክብሮታል የሳኦል አቀራረብና የናቡከደነጾር ሁኔታ የሚለያይበት ነጥብ ቢኖርም በመስገዳቸው አልተወቀሱበትም ። እኛም በሌላ ኃጢአታችን ልንወቀስ ይገባል እንጂ ለቅዱሳን ሰዎች የጸጋ ስግደት በማቅረባችን እንወቀስበትም ቅዱሳንም ሆኑ ፈጣሪያቸው እግዚአብሔር የጸጋ ስግደት ለምን አቀረባችሁ ብለው የወቀሱበት ጊዜ የለም ። የጸጋ ሰጊድ ማቅረብ ተገቢ ስለኾነ ቢያስመሰግን እንጂ አያስወቅስም ።

ሠ/ ዘፍጥ ፴፯ ፡፩-፲፩ ና ዘፍጥ ፵፪ ፡፯ና፱ ዘፍጥ ፵፫ ቁ፳፮ -፳፰ ን ብንመለከት ለዮሴፍ ወንድሞቹ እግዚአብሔር ባሳየው ራእይ መሠረት የጸጋ ስግደት አቅርበውለታል ። ይኸው በእግዚአብሔር ፈቃድ የተፈጸመ መኾኑን ያስረዳናል ። ታላላቆች ለታናሽ ወንድማቸው መስገዳቸው ከእግዚአብሔር ስለተሰጠው ጸጋ እንደኾነ ተገንዝበን እኛም በጸጋ ለከበሩ ቅዱሳን ይልቁንም ለአምላካችን እናት ጸጋን የሞላብሽ ሆይ እያልን የአክብሮት (የጸጋ ስግደት) እናቀርባለን ። ወንድሞቹ ለዩሴፍ ከሰገዱ ያም የእግዚአብሔር ፈቃድ ከኾነ እኛ የማንሰግድበት ምክንያት ምን ይኾን? አጎንብሰውም ሰገዱለት ይላል እኛም አጎንብሰን ለቅዱሳን ሁሉ እንሰግድላቸዋለን ።

# ስግደት ለማን? ለምን?

ካለፈው የቀጠለ

ስግደት ለማን? ለምን? በሚል ርዕስ በአራት ተከታታይ ይዘት ያቀረብንላችሁን መሠረታዊ የሆነውን ከአንባቢ የተላከ ጥያቄና መልስ ጽሑፍ በዛሬው እትም የመጨረሻውን ክፍል በማጠቃለል አቅርበናል።

፪ኛ ከጠያቂው ፩ኛ ራእይ ፫፡ ፳-፱ ለፊላደልፍያ ቤተክርስቲያን የተነገረ ነው የተናገረውም እግዚአብሔር ወልድ ነው፤ በንግግሩም በእጅ የታዩት ሰባት መቅረዞች ፯ቱ አብያተ ክርስቲያናት መሆናቸውን ገልጾ በዮሐንስ በኩል ለ፯ ቤተክርስቲያን መልእክቱን ተግሳፁንና ምክሩን ሲያስተላልፍ እናነባለን፤ ራእይ ፩፡፲፯-፳ ምናልባት በመጽሔቷ የተሰጠው መልስ «መልአክ» የሚለው በመጠቀሱ ከሆነ በመሠረቱ ለየቤተክርስቲያናት የተመደቡ መላእክት እንደሌሉ ይታመናል፤ እዚህ ላይ ጌታ ለዮሐንስ ለፊልድልፍያ ቤተክርስቲያን መልአክ ማለቱን በጥሬው ካልወሰድን በስተቀር እራሷን ቤተክርስቲያኗን እንጂ መልአክን ስላለመሆኑ፤

ሀ/ በራእይ ፫፡፲ «ትዕግሥተኛ ሁን ያልሁህን ቃሌን ጠብቀህ እኔም በምድር ላይ የሚኖሩትን ሊፈት ናቸው በዓለም ሁሉ ላይ ከሚመጣው ከመከራ ሰዓት አድንሃለሁ» የተ ባለለት ለቤተክርስቲያን ይሆን ለመልአክ ነው ለማለት እጅግ ይከብዳል፤ የዓለምና የምድር ሥራ ከመላእክት ተግባር ጋር አይገናኙምና።

ለ/ በራእይ ምዕራፎች ፪ እና ፫ የተጻፈላቸው ፯ቱ ቤተክርስቲያናት ሁሉ /ለእያንዳንዳቸው/ መልአክ የሚል የስያሜ ቃል የተጻፈ ሲሆን ለአብዛኞቹ ቤተክርስቲያናት ነቀፌታው ተግሣፅና ማስጠንቀቂያ የተጻፈው ለመላእክት ነው ብለን ከተቀበልን መላእክት በምድራዊው የሰው ክፉ ሥራ በሚመጣው የፍርድ ቀን ይቀጣሉ ማለት ነው?

በእኔ እምነት በራእይ ፫፡፰-፱ «ሐሰተኞች ሆነው ሳለ እውነተኞች ነን የሚሉትን እነዚያን ከሰይጣን ማኅበር የሆኑትን ውሸታሞች መጥተው እውነተኛ እምነት ተከታይ በሆነችው በቤተክርስቲያን ሥር እንዲወድቁ አደርጋቸዋለሁ» ብሏል፤ የቤተክርስቲያን ራስ ደግሞ ጌታ ኢየሱስ ነው። ለፍጡራን /ለቅዱሳን/ ስግደት የአምልኮም ይሁን የክብር ይገባቸዋል ተብሎ በመጽሔቱ ለተጠቀሰው ለማገና ዘቢያነት የተሰጡት ጥቅሶች ይህን ሲያረጋግጡ ስላላገኘኋቸው ወይም ሌላ የተለየ መልእክት ስላላቸው ማገናዘቢያነታቸውን ያልተቀ በልኳቸው ከመሆኑ በላይ በአንጻሩ «ስሙ ቀጥተኛ የሆነው እግዚአብሔር ቅንአት ያለው አምላክ ነውና ለፍጡራን ቅዱስም ይሁን እርኩስ ለማንም ለምንም «አትስገድላቸው፤ አትቀበሏቸው፤ አትከተሏቸው ብሎም አታ ምልኳቸው» በማለት ያስጠነ ቅቃል፤

ማረጋገጫ ዘጸአት ፳፡ ፫-፮

ዘጸአት ፴፬፡ ፲፬-፲፯

ዘዳግም ፮፡ ፲፬-፲፭ ተብሎ ማስተባበያ ለቀረበው

፪ኛ/ ከአዘጋጆች፤ ለማረጋገጫ የተጠቀሱት ጥቅሶች የአምልኮት ስግደት ወይም የባሕርይ ስግደት ለፈጣሪ ብቻ እንጂ ለፍጡራን ሊቀርቡ እንደማይገባ ከማስረዳት በስተቀር የጸጋ ስግደትን ለመቃወም የተናገሩ አለመኾናቸውን ተመልከት ልን። እኛም የምናምነው የአምልኮት ስግደት መመለክ የባሕርይ ገንዘቡ ለሆነ ለፈጣሪያችን ብቻ እንደሚቀ ርብ ለፍጡር እንደማይሰጥ ፀውቀን ይኸንኑ ጠንቅቀን እንጠብቃለን። የጥቅሶቹ መሠረታዊ ጽንሰ ሐሳብ አመጣጡ ይኸ ሆኖ ሳለ ለቅዱሳን የጸ ጋ ስግደት በምናቀርብ ክርስቲያኖች ላይ ጣዖት እንደሚያመልኩ አሕዛብ ገምቶ ያለአግባብ መጥቀስ እውነትም ከአለማስተዋል የመነጨ ትችት ነው ከማለት አድርሶናል።

ከላይ ስናብራራ እንደቆየነው ሎጥ ለሁለቱ መላእክት፤ ዮሴፍ ወንድሞች ለዮሴፍ፤ ዮሴፍ ለአጐቱ ለኤሳውና ለአባቱ ለያዕቆብ እንደሰገዱለት ያለ የጸጋ ስግደት ለቅዱሳን ይቀርብላቸዋል እንላለን እንጂ ፤ቅዱሳን ይመለካሉ ወይም የአምልኮት ስግደት ይቀርብላቸዋል አላልንም። እንኳን በጽሑፍ ባሳባችንም የሌለ ነገር ነው። «አትቀበሏቸው አትከተሏቸው» ያለው ጣዖታትን፤ በጣዖት ላይ ያደሩ ርኩሳን መናፍስትን ወይም የሐሰት አማልክትን እንጂ የጸጋ ጌትነት፤ የጸጋ አምላክነት ያላቸውን ቅዱሳንን አለመሆኑን ጠያቂው በውል ሊረዱት ይገባል።አእም ሮውን ሳይዘጋ በቅንነት ለመረዳት ለሚፈልግ አንድ በአንድ በደስታ ከማብራራት ወደ ኋላ አንልም። ቅዱሳንንማ ማምለክ አይገባም እንጂ መቀበልም መከተልም ይገባል ጌታችን ሐዋርያትን እናንተን የተቀበለ እኔን ይቀበላል ለምን አላቸው? ቅዱሳን ሐዋርያትን መቀበል በእነርሱ ያደረውን ጌታ ክርስቶስን መቀበል ስለኾነ አይደለምን? ጣዖትንም ጣዖታ ውያንን ግን ተቀበሉ አላለንም እኛም ብንሆን አስመሳዮች ወንጌላውያን ነን፤ ሐዋርያት ነን እያሉ የሚመጡ ቢጽ ሐሳውያንን እንቃወማለን እንጂ አንቀበልም። እነርሱን እንኳን ልንቀበል ሰላምም አንላቸውም ምክንያቱም የክፋታ ቸው /የዓመፃቸው የክህደታቸው/ ተባባሪ እንዳንሆን ነው። /ማቴ ፲ ቁ ፵-፵፩ ፪ቆሮ ፲፩፡፲፫-፲፭/ ።

ቅዱስ ጳውሎስም ጢሞቲዎስን አንተ ግን ትምህርቴንና አካሄዴን አሳቤንም እምነቴንም ትዕግሥቴንም ፍቅሬንም መጽናቴንም ስደቴንም መከራዬንም ተከተልህ» /፪ ጢሞ ፫ ቁ ፲-፲፩/ ለምን አለው ቅዱሳንን መከተል ተገቢ መኾኑን ሲገልጽለት አደለምን? ቅዱሳንን ስንከተል ገድላቸውን፤ ትሩፋታቸውን ሁሉ በመከታተል መኾኑን ተገንዘብ ራእይ ፫ ቁ ፮ ፱ የተጠቀሰው ለቅዱሳን ሰዎች ለጻድቃን ለሰማዕታት /የጸጋ ስግደት እንደሚገባቸው ለማስገንዘብ ነው እንጂ፤ በራእይ የተገለጸው መልአክ የተባለው፤ በቁሙ መልአክ የተባለው ነው ማለታችን አይደለም።



www.ethiopianorthodox.org

ጥቅሶች ለምን ለምን ማስረጃ እንዲሆኑ እንዳቀረብናቸው ከማብራሪያ ጋር አገናዝቦ መረዳት ሲገባ ብዙ ሐተታ ማተም ባላስፈለገ ነበር። ከሆነም መልሱን እንደሚከተለው እናቀርባለን።

በራእይ ፩ ቁ ፳ ላይ ለዮሐንስ የተገለጸው ክርስቶስ በቀኝ እጁ ያየኋቸው የሰባቱ ከዋክብትና የሰባቱ የወርቅ መቅረዞች ምሥጢር ይህ ነው፤ ሰባቱ ከዋክብት የሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት መላእክት ናቸው። ሰባቱም መቅረዞች ሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት ናቸው» ብሎ በእስያ ስለተመሠረቱት አብያት ክርስቲያናት መሪዎቻቸው /አለቆቻቸው/ አስረድቶታል በ፯ ከዋክብት የተመሰሉት የ፯ቱ አብያተ ክርስቲያናት ኤጲስ ቆጶሳት ናቸው መላእክት ማለት አለቆች ማለት ነው። የቤተክርስቲያን መሪዎች ኤጲስ ቆጶሳት ሆነው እንደሚሾሙ በቅዱስ መጽሐፍ የታወቀ ስለኾነ ብዙ ሐተታ አያስፈልገውም።

/፩ጢሞ ፫ ቁ ፩-፭ የሐዋ ሥራ ፳-፳፰/ ጳጳሳት ኢጲስ ቆጶሳት የቤተክርስቲያን አስተዳዳሪዎች የምዕመናን ጠበቆች ናቸው ዛሬም ቢሆን በየደረጃው በየማእረጋቸው ያሉ የቤተክርስቲያን መሪዎች ወይም አስተዳዳሪዎች በቤተክርስቲያናችን የእልቅና ማዕረግ አላቸው። አለቃ እገሌ ወይም መልአክ ገነት መልአከ ኃይል፣ መልአከ አሚን ወዘተ... እየተባሉ በየማዕረጋቸው ይጠራሉ።

በእስያ ባሉ ፯ አብያተ ክርስቲያናት የተሾሙት ኤጲስ ቆጶሳት መላእክት መባላቸው አለቆች መኾናቸውን ለማመልከት ነው እንጂ በቁሙ መላእክት ናቸው ማለት አይደለም በግእዙ መዝሙረ ዳዊት በመዝ ፪ ቁ ፪ ላይ «ወመላእክት ተጋብኡ ምሳሌሆሙ ኅቡረ» ያለውን በአማርኛው መዝሙረ ዳዊት «አለቆችም» ተብሎ ተተርጉሟል። በመዝ ፷፯/ ፷፰/ ቁ ፳፯ ላይም «መላእክተ ይሁዳ መሳፍንቲሆሙ መላእክቱ ዘብሎን ወመላእክቲኒ ንፍታሌም» ተብሎ በግእዙ የተጻፈው በአማርኛው መዝሙር «የይሁዳ አለቆች ከሠራዊታቸውን ጋር ለየዛብሎን አለቆችና የንፍታሌምም አለቆች ተብሎ ተተርጉሟል ሌላም ይህን የመሰለ መረጃ ሞልቷል። ከራእይ ምዕ ፪ እስከ ፫ ድረስ በኤፌሶን ወደ ቤተክርስቲያን መልአክ ጻፈ እስከሚለው ድረስ የእገሌ ቤተክርስቲያን ፯ቱ መንፈሳውያን ከዋክብት ወይም ኤጲስ ቆጶሳት መኾናቸውን ማስተዋል ይገባል። ኤጲስ ቆጶሳቱን መላእክት ማለቱ የቤተክርስቲያን አለቆች አስተዳዳሪዎች ወይም ጠበቆች ሲላቸው ነውና ትርጓሜውን መገንዘብ ያስፈልጋል።

በቤተክርስቲያናችን ታሪክ እንደሚነገረው የ፯ቱም አብያተ ክርስቲያናት አለቆች ስሞቻቸው ታውቋል። እያንዳንዳቸው እንደሐዋርያት ሁለት ሁለት ስም አላቸው ስምኦን ጴጥሮስ ወይም ኬፋ፣ ዮሐንስና ያዕቆብ ወልደ ነጎድጓድ ቶማስ ዲዲሞስ ተብለው እንደሚጠሩ ሁሉ እነዚህም ፯ቱ ኤጲስ ቆጶሳት መንታ መንታ (ጥንድ) ስም አላቸው።

የቤተክርስቲያኑ ስም የኤጲስ ቆጶሱ የአለቃው

ዮሐንስ ሁለተኛ ስሙ ደማትሬ

፩ የኤፌሶን ቤተክርስቲያን ሄሬኔዎስ ሁለተኛ ስሙ ኢያሳ

፪ የሴሚርኔስ ቤተክርስቲያን ጋይዩስ ሁለተኛ ስሙ ጠብዶን

፫ የጴርጋሞን ቤተክርስቲያን ጋይዩስ ሁለተኛ ስሙ ጠብዶን

፬ የትያጥሮን ቤተክርስቲያን ሉክኖስ ሁለተኛ ስሙ ዴጀባል

፭ የስግዴሲሶን ቤተክርዕቲያን አርስጦን ሁለተኛ ስሙ ርሄል

፮ የሉደቅያ ቤተክርስቲያን አርከቦስ ሁለተኛ ስሙ ጋብጋብኤል

፯ የፊልድልፍልያ ቤተክርስቲያን ድሜጥሮስ ሁለተኛ ስሙ ፌቤፌል

፯ቱ አብያተ ክርስቲያናት በእስያ ያሉ አገረ ስብከቶች ወይም መንበረ ጵጵስና መኾናቸው ነው።

የቤተክርስቲያን ራስ ኢየሱስ ክርስቶስ ለፊልድልፊያው ቤተክርስቲያን አለቃ /ኤጲስ ቆጶስ/ ለድሜጥሮስ የጸጋ ስግደት በጠላቶች ሳይቀር እንደሚቀርብለት በማስረዳት ልዩ ክብርን አጎናጽፎታል። ለድሜጥሮስ እንዲሰገድለት ጸጋን የሰጠው ራሱ ክርስቶስ መኾኑን በራእይ ፫ ከቁጥር ፯-፱ ተጠቅሷል። «እነሆ መጥተው በእግሮችህ ፊት ይሰግዱ ዘንድ እኔም እንደ ወደድሁህ ያውቁ ዘንድ አደርጋቸዋለሁ» /ቁ ፱/ ያለውን ቃል አስተውለህ ክርስቶስ ለወደደው የጸጋ ስግደት እንዲቀርብለት ማድረጉን ተገንዘበ።

፫ኛ/ ከጠያቂው «በተጨማሪም መላእክት እራሳቸው ስግደት ከሚገባው አምላክ ጋር እንዳይጋጩ ከነቢያት ጋር አብረን የእግዚአብሔር ባሪያ ነንና ለእኛ አትስገድ ለእግዚአብሔር ብቻ ስገድ» እያሉ

## መለከት አንድ ልደት አስቆጠረች

መ ግዜ ዘኖናስ ቃለ እግዚአብሔር
ለ ተዋኀዶ ልጆች የማይለውጥ ክብር
ከ ዳር እስከዳር አስተማርሽን
ት ምህርተ እምነትን አሳወቅሽን
አ ዎ መለከት እንዲህ በማለት ጠራሽን
ን ሁ ደቀቅየ አስምሩ እውነትን
ድ ል እንድትመቱት ጠላታችሁ ሰይጣንን
ል ሁል የመሠረተሽ በወርሃ ኅዳር
ደ ግ ነውና ይስበክ ዘንድ ቃለ እግዚአብሔር
ት ሂዚ ዘንድ ምኞቱ ነውና እስከመጨረሻው በማስተማር።
አ ስቆጠርሽ በእውነት ያለ ሐሰት

ዲ/ሲ/ን ወልድ ክፍሌ
ከደ/ገ/ቅ/ አማኑኤል ካቴድራል።



www.ethiopianorthodox.org

በማረጋገጫ፡ ቆላስየስ ፪፡ ፲፰-፲፱ በራእይ ፲-፲፱ በራእይ ፳-፳፪ በዕብ ፩፡ ፲፬ ላይ እያስጠነቀቁና እየተከላከሉ እያየን የለም የአምልኮ ሳይሆን የክብር ስግደት ይገባችኋል ብለን መፋለም ያለብን አይመስለኝም፣ ምክንያቱም በእነዚህ ጥቅሶች ዮሐንስ ያቀረበው ስግደት ለእግዚአብሔር ሳይሆን ያን የመሰለ ራእይ በማየቱ ተደናግጦ ሊሆን ይችላል፣ ይህም ካልሆነ እንደ መጽሔቷ እምነት ለመልአኩ ክቡር እንደሆነ አድርገን ብንቀበለውም መልአኩ ራሱ ሊሰገድለት እንደማይገባ አስጠንቅቆ ለተፈጸመው ስህተት ማረሚያ ምክርና ተግሳጽ ሰጥቷል።

ዮሐንስም ማረሚያውን ተቀበለ እንጂ አልተፋለመም መሆን የሚገባውንም ጽፎ ለእኛ አስተላለፈልን ይህን ዓይነት ስሕተት ሲፈጸም በተመሳሳይ ግሳጼ ማረሚያ የተሰጡባቸው በርካታ ሥፍራዎች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ይገኛሉ። እግዚአብሔር፣ ስግደት የአምልኮ መግለጫ መሆኑን ተናግሯል ዘጸአ ፳፡፭ አታምልክ አትስገድለትም በማለት ሁለቱ የማይነጣጠሉና በቅደም ተከተል ያሉ አንዱ ሌላውን የሚገልጽ መሆኑን ያሳያል፤ መስዋዕት ማቅረብና ስግደት የአምልኮ መግለጫ መዛሪያዎች /መንገዶች/ ናቸው።

ከላይ ለመጥቀስ እንደተሞከረው መላእክትና ጻድቃን ለቀረበላቸው ስግደት «ተው ይህን አታድርግ እኔ ከአንተና ከነቢያት ጋር የዚህን መጽሐፍ ቃል ከሚፈጽሙ ሰዎች ጋር አብሬ ባሪያ /አገልጋይ ነኝ ለእግዚአብሔር ስገድ በማለት ስግደት የሚገባው ለማን እንደሆነ ቁልጭ አድርገው ገልጸዋል። በተለይ የዚህን መጽሐፍ ቃል ከሚፈጽሙ ሰዎች ጋር ማለታቸው ጻድቃን ስግዕታትን ማርያምን ወዘተ በማጠቃለል ስግደት እንደማይገባቸው በይበልጥ ጥርትና ቁልጭ አድርገው አብራርተዋል።» ተብሏል።

፪ኛ/ ከአዘጋጆች ከቆላ ፪ ቁ ፲፰-፲፱ የተጠቀሰው ሙሉ ቃሉ እነሆ «ትሕትናንና የመላእክትን አምልኮ እንደወደደ ባላየውም ያለ ፈቃድ እየገባ በሥጋዊም አእምሮ በከንቱ እየታበየ ማንም አይፍረድባችሁ። እንደዚህ ያለ ሰው፣ ራስ ወደሚሆነው አይጠጋም። ከእርሱም አካል ሁሉ፣ በጅማትና በማሰሪያ ምግብን እየተቀበለ እየተጋጠመም እግዚአብሔር በሚሰጠው ማደግ ያድጋል» ይላል ቅዱስ ጳውሎስ ይህን መልእክት የጻፈው ከክርስትና ወደ አይሁ ዳዊነት ክርስቲያን መስለው ምዕመናን፣ ክርስቶስን ለመገልበጥ በወንጌል ፋንታ ኦሪትን፣ በጥምቀት ፋንታ ግዝረትን በክርስቶስ ፋንታ ሥርዓት የለሽነትን ስለሚከታተሉም የፈሪሳውያንን ወግ ስለሚከተሉ ቢጽ ሐሳውያን /ዩዛዩዞንዲስ/ ስለተባሉ መናፍቃን አሳሳችነት ለቁላስይስ ክርስቲያኖች ሊያስጠነቅቅ እንደሆነ በቅድሚያ መገንዘብ የነገሩን አመጣጥ ለመረዳት ያስችላል።

የጥቅሱን ንባብ ከኦርቶዶክሳዊው የግእዝና አማርኛው ነጠላ ትርጓሜ ሐዲስ ኪዳን እንደሚከተለው አቅርበነዋልና ንባቡን ለማስማማት ይረዳናል። «ወአልቦ ዘያስተአብ ደክሙ በእንተ ሥጋሁ ለክርስቶስ ፈቂዶ በተየውሆ ወበተናሕስዩ ርእስ ከመትእዛዙ ለኅርመተ መላእክት በዘኢርእየ ወይትሜካሕ በከንቱ በምክረ ሥጋሁ «ወኢይጸንዕ በርእጸ ዘቦቱ የኅድር ኵሉ ሥጋ ወይትዋደድ በአሥራው ወመሌሊት ወይልሕቅ ወይጸንዕ ወይበዝኅ ወይመልእ በእግዚአብሔር» «ስለ ክርስቶስ ሰው መሆን የሚያስንፋችሁ አይኑር በመታለል ራስን ዝቅ በማድረግ ለሰው ሠራሽ ሥርዐት እንድትታዘዙ ሽቶ ባላየው በሥጋው አሳብ በከንቱ በሚመካ ገንዘብ ሥጋ ጸንቶ በሚኖርበት በሥር በጅማት በሚስማማበት በእግዚአብሔር በሚያድግበት በሚጸናበት በሚመላበትና ፍጹም በሚሆንበት በራስ አይጸናም» የግእዙም የአማርኛውም ንባብ ይኸው ነው። «ትሕትናንና የመላእክትን አምልኮ እየወደደ» ከሚለው ንባብ ይልቅ «ከመትትአዘዙ ለሕርመት መላእክት ለሰው ሠራሽ ሥርዓት እንድትታዘዙ ሽቶ» የሚለው ምሥጢር አያፋልስም እንዴት እንደሆነ «ትሕትናን እየወደደ የመላእክትን አምልኮ እየወደደ» ሲል ክርስቲያንማ ትዕቢትን ሳይሆን ትሕትናን መውደድ ይገባዋል።

ራሱ ቅ/ጳውሎስም በሮሜ ፲፪ ቁጥር ፲፮ ላይ «የትዕቢትን ነገር አታስቡ ነገር ግን የትሕትናን ነገር ለመሥራት ትጉ» ብሎ ይመክራል ጌታም «ከእኔም ተማሩ እኔ የዋህ በልቤም ትሑት ነኝና ለነፍሳችሁም ዕረፍት ታገኛላችሁ» /ማቴ ፲፩ ቁ ፳፱/ ይላል። በአቀማመጥ እንኳን ትሕትና እንድናሳይ መክሮናል ትሕትናውንም ዝቅ ብሎ የደቀመዛሙርቱን እግር በማጠብ የትሕትናን ሥራ እንደሠራ አርአያውን አሳይቶናል። /ሉቃ ፲፬ ቁ ፯-፲፩ ዮሐ ፲፫ ቁ ፲፪-፲፮/ ትሕትናን መውደድ ምን ያስነቅፋልና ነው ቅዱስ ጳውሎስ ትሕትናን እንደነቀፈ አድርጎ ማስመሰል፤ ለመላእክት የጸጋ ስግደት አይቀርብም እንዳንልማ ሎጥ ለሁለቱ መላእክት ኢያሱ ለመላእክት አለቃ ለቅዱስ ሚካኤል መስገዳቸውን አስረድተናል።

የመላእክት አምልኮ እየወደደ» የሚለውንም እንመርምር የመላእክት አምልኮ ማለት መላእክት የሚያመልኩት ማምለክ ማለት ነው የመላእክት አምልኮ ምንድነው ወይስ መላእክት አምልኮታቸው ምንድነው የሚያመልኩት ማንን ነው? መላእክትማ ለክርስቶስ ይሰግዳሉ። እግዚአብሔርነቱን ዐውቀው ይሰግዱለታል። ያመልኩታል። /ዕብ ፩ ቁ፮ መዝ ፺፮፡፯ ራእይ ፭ ቀ ፲፩-፲፬/

የመላእክት አምልኮ ማለት ለእግዚአብሔር መስገድ ማለት ከሆነ አምልኮታቸውን መንቀፍ እንዴት ይቻላል? ከነቀፍንማ ለክርስቶስ አንስግድም ማለታችን ነው። የቤተክርስቲያን ራስ ከሆነው ከእርሱ ጥግነት /ረድኤት ጸጋ/ መለየት ይሆንብናል። ይህንን ለማለት የፈለግንበት ምክንያት ንባቡ በትክክል ካልተተረጐመ ማሳሳቱን ለማሳየት ነው።» ንባብ /ፊደል/ ይገላል መንፈስ /ትርጓሜ/ /ግን ያድናል ፪ኛ ቆሮ ፫ ቁጥር ፮/ የተባለው ስለዚህ ነው። በፊደል የተመሰለችውን ኦሪትን ብቻ በማንብንብ የሚዳን መስሏቸው ከመንፈስ /ከሕይወት ሰጭ ወንጌል/ ተለይተው ሞተ ነፍስ ስለደረሰባቸው ይሁዳዎች / ቢጽሐሳውያን/ የተነገረት ነው። ዛሬም ቢሆን መጽሐፍ ቅዱስን ከመጽሐፍተ ሊቃውንት ቤተክ



www.ethiopianorthodox.org

ርስቲያን ትርጓሜ ጋር በማስተያየት ከመምህራን እየጠየቅን ካልተረዳን ማነብነብ ችለናል ብለን ንባቡን ብቻ ብንከታተል ከእንዲህ ዓይነቱ የምሥጢር ስህተት ያደርሰናል። ወደ ትክክለኛው የንባቡ አተረጓጎም እንመለስና እናጢነው። «የመላእክት አምልኮ የተባለው መላእክትን ማምለክ ኑሮ የተጻፈ አይደለም እኛ ክርስቲያኖች ነን መላእክትን እናከብራለን እንጂ አናመልካቸውም ያንጊዜም ቢሆን መላእክትን የሚያመልኩ ሰዎች ኑረው እነዚያን ለመንቀፍ የጻፈው አይደለም መላእክት የተባሉት የአይሁድ ረበናት ወይም አለቆች ናቸው።

እነዚህ የአይሁድ መምህራን /ረበናት/ ወይም አለቆች ከእግዚአብሔር ቃል ጋር የማይጣጣሙ ሰው ሠራሽ የአምልኮት ሥርዓት ነበራቸው ቅዱስ ጳውሎስ የእነርሱን ሥርዓተ ረበናት ደኅና አድርጎ ያውቀው ነበርና ክርስቲያኖች ለእነዚህ ከንቱ ሰው ሠራሽ ትእዛዝ ተገዢ ሁነው እንዳይዋረዱ ለማስጠንቀቅ ጽፎላችዋል። ትሕትና ያለው «ለሥርዓተ ረበናት መገዛትን» መሆኑን በማስተዋል የመላእክት አምልኮ የሚለውን ንባብ ተመልከተን ከመሳሳት እንጠበቅ ሕርሙተ መላእክት ማለት ሰው ሠራሽ የሆነ የረበናት የአምልኮ ሥርዓት መሆኑን /ማቴ ፲፭፣ ፩-፭ ማር ፯፣ ቁ ፩-፳፫/ ራእይ ፲፱ ቁ ፲ና ራእይ ፳፪ ቁ ፰-፱ ያሉትን ጥቅሶች ለመመርመር ከእኛው ከኦርቶዶክስ ሐዲስ ኪዳን የአማርኛውን ብቻ ንባብ እናመለክታለን። «ከእግሩ በታች ወድቄ ሰገድሁለት እንዲህም አለኝ ተጠንቀቅ አትስገድልኝ፤ እኔም እንደ አንተ ከአንተ ጋር የኢየሱስን ሕግ ከሚጠብቁት ከወንድሞችህም ጋር አገልጋይ ነኝና ነገር ግን ሁላችን ለእግዚአብሔር እንስገድ የትንቢት መንፈስ የኢየሱስ ምስክር ነውና።»

«ይህን የሰማሁ ያየሁ እኔ ዮሐንስ፤ ይህን በአየሁ በሰማሁ ጊዜ ያን ጊዜ ይህን በአሳየኝ በዚያ መልአክ እግር ስር ሰገድኩ እሱ ግን እንዲህ አለኝ ዕወቅ ለእኔ አትስገድ እኔም እንዳንተ ባርያ ነኝ፤ እንደወንድሞችህ ነቢያትም የዚህን መጽሐፍ ቃል እንደሚጠብቁ ምእመናንም፤ አንተስ ለእግዚአብሔር ስገድ» ይላል።

ለቅዱስ ዮሐንስ የተገለጸለት መልአክ ሁለት ጊዜም ቢሰግድለት አትስገድልኝ ብሎታል። ዮሐንስ ለመልአኩ የሰገደው ደንግጦ ነው ወይስ ተሳስቶ እንደ እኛ እምነትም ሆነ እንደመጽሐፉ አካሄድ ወልደ ነጎድጓድ ቅዱስ ዮሐንስ ለመልአኩ የሰገደው ደንግጦም ነው ተሳስቶም ነው አንልም ደንግጦም ተሳስቶም ነው እንዳንል ለመልአኩ ደንግጬ ሰገድሁለት መልአኩ መሆኑን ባለማወቅ ተሳስቼ ወይም ለመልአኩ ስግደት የሚገባ መስሎኝ ሳላውቅ በመፈጸሜ ዕርማት ቀረበብኝ ስለዚህም ለወደፊት ለመልአክ የጸጋ ስግደት ማቅረብ አይገባም አላለም መልአኩም አትስገድልኝ እኔ እንደ ወንድሞችህና እንደ ነቢያት የመጽሐፉን ቃል እንደሚጠብቁ ምእመናን አገልጋይ ስለሆንኩ ለእግዚአብሔር እንስገድ ለእግዚአብሔር ስገድ አለው እንጂ የሰገድህልኝ መልአክ መሆኔን ባለማወቅህ ወይም ለመልአክ የጸጋ ስግደት እንደማይገባ ባለመረዳትህ በስሕተት ስለሆነ መታረም አለብህ አላለውም። ተጠንቀቅ፤ ዕውቅ በማለትና ታረም፤ ተሳስተሃል በማለት መካከል ያለው ልዩነት በጣም ሰፊና የማይመሳሰል ነው።

መልአኩ አትስገድልኝ ማለቱ የዮሐንስን ክብር ሊገልጽለት ወዶ ነው ዮሐንስ በንጽሕናው ከመላእክት ማዕረግ ስለደረሰና በማዕርገ ክህነቱም ከመላእክት በላይ የሚያደርገው ጸጋ ስለተሰጠው ሐዋርያት ወንድሞችህም ሆኑ ነቢያት የእግዚአብሔርን ቃል እንደእናንተ የጠበቁ ምዕመናንም ቢሆኑ በብቃት ከእኛ ከመላእክት ማዕረግ ስለደረሳችሁ ንጹሐን ስለሆናችሁ ከእኛ የሚበላልጥ ለእኔ መስገድ አይገባህም አንተም እንደኔው የእግዚአብሔር ፈቃድ ፈጻሚ ተገዥ ነህ ለማለት የተናገረው ነው። መልአኩ ዮሐንስን ለማክበር የተናገረው ቃል እንጂ ዮሐንስን ለመገሰጽ አለመሆኑን እናምናለን። ምክንያቱም ዮሐ

## የሁለተኛ ዓመት ቁጥር ፩ ጥያቄዎች

፩. በኦሪት ዘፍ ም ፫ ቁ ፳፩ «እነሆ አዳም መልካምንና ክፉን ለማወቅ ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ።» የሚለው ጥቅስ ስለማን እንደተነገረ ያብራሩ?

፪. የእግዚአብሔር ቃል ከሥጋ ከተዋሐደ በኋላ ምን ምን ስሞችን ተሰጡት እነዚህስ ስሞች ብቻ ለቃል ወይም ለሥጋ ይነገራሉን? ለምን?

፫. መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሁለት ልደት እንዳሉት ይታወቃል እነዚህን አብራርተው ይጻፉ።

፬. ከተዋሕዶ በኋላ መለኮትና ትስብእትን መለየት ይቻላልን? ይህንኑ በምሳሌ የብራሩት።

፭. ሀ, «የሚያስተውሉ የገላትያ ሰዎች ሆይ በዓይናችሁ ፊት ኢየሱስ ክርስቶስ እንደተሰቀለ ሆኖ ተስሎ ነበር ለእውነት እንዳትታዘዙ አዚም ያደረገባችሁ ማን ነው?» ይህ ጥቅስ በቅዱስ መጽሐፍ በየትኛው ምዕራፍና ቁጥር ይገኛል።

ለ, «ቃሉን የምታደርጉ ሁኑ እንጂ ራሳችሁን እያሳታችሁ የምትሰሙ ብቻ አትሁኑ።»

ይህ ጥቅስ በቅዱስ መጽሐፍ በየትኛው ምዕራፍና ቁጥር ይገኛል።

ሐ/ መድሐኒታችን ወደ ፊሊጶስ ቂሳርያ በደረሰ ጊዜ ስለማንነቱ ምን ሲል ደቀመዛሙርቱን ጠየቀ እነሱስ ምን ብለው መለሱለት ይህ ታሪክ በቅዱስ መጽሐፍ በየትኛው ምዕራፍ ቁጥር ይገኛል።

መ/ «ስለ ምድራዊ ነገር በነገርኋችሁ ጊዜ ካላመናችሁ ስለ ሰማያዊ ነገር ብነግራችሁ እንዴት ታምናላችሁ?» ከሰማይም ከወረደው በቀር ወደሰማይ የወጣ ማንም የለም እርሱም በሰማይ የሚኖረው የሰው ልጅ ነው።» ይህ ታሪክ በቅዱስ መጽሐፍ በየትኛው ምዕራፍና ቁጥር ይገኛል።

መልካም የልደት በዓል ይሁንላችሁ።





www.ethiopianorthodox.org

ንስ በንጽሕናው ራእይና ምሥጢር የተከሰተለት ከዚያም በላይ ለክዊነ እሳት ማዕረግ ለነጽሮተ ሥሉስ ቅዱስ የደረሰ ፍጹም ሐዋርያ ነው ቅዱሳን ከንጹሕ ልቡና ማዕረግ ሲደርሱ እግዚአብሔርን ከማየት ይደርሳሉ። ምንም የእግዚአብሔርን ረቂቅ ባሕርያትን ማየት ባይቻላቸው እሱ በፈቀደው መገለጥ ያዩታል። ይኸውም ተከስቶ ይባላል። ቅዱስ ጳውሎስ ተከስቶን መገለጥ ብሎታል /ማቴ ፭ ቁ ፰ ፪ኛ ቆሮ ፲፪ ቁ ፩/ ቅዱስ ዮሐንስ በድንግልና በንጽሕና ተወስኖ የሚኖር ቅዱስ ሰው ነው። ኋላ በትንሣኤ ጊዜ ጻድቃን እንደመላእክት ያለ ጋብቻ ልዩ በሆነ መንፈሳዊ ሕይወት በተሐድሶ ጸንተው እንደሚኖሩ በቅዱስ ወንጌል ታውቋል። ጌታችን ይህንን የሰማያዊ ሕይወት አኗኗር ሲገልጽ በትንሣኤስ እንደ እግዚአብሔር መላእክት በሰማይ ይሆናሉ እንጂ አየገቡም አይጋቡምም። /ማቴ ፲፪ ቁ ፴/ ማለቱ የመላእክት አኗኗርና የቅዱሳን ሕይወት የሚገናዘብ መሆኑን ለማስረዳት ፈልጐ ነው። ያንን ዓይነቱ ኑሮ በዚህ ዓለም የሚለማመዱ ቅዱሳን አሉ ከእነዚያ መካከል በድንግልና ሕይወቱ የተመሰከረለት ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ ይገኛል። ስለዚህ ነው በቅዳሴያችን ተውህቦ ድንግልና ለዮሐንስ ተሰጠው ብለን የምናዜመው የሐዋርያት ማዕረጋቸው እጅግ ከፍ ያለ ነው። ቅዱስ ዮሐንስ ከ፲፪ቱ ቅዱሳን ሐዋርያት አንዱ ነው ሐዋርያው ጳውሎስ እንዳስተማረን መላእክትን ለመዳኘት የሚያስችል ጸጋ ለቅድሳን እንደተሰጣቸው ተረድተናል። /፩ኛ ቆሮ ፮ ቁ፫/ «ወኢተአምኑኑ ከመ መላእክት ጥቀ ንኴንን ኅድጉሰ ዘዝዓ ለም የዚህን ዓለም ዳኝነት ተውትና መላእክትን ስንኳ እንድንገዛ አታውቁምን» ማለቱ ለካህናተ ወንጌል ለሐዋርያት የተሰጣቸውን ያገኘ ማዕረግ ያስረዳናል።

መልአኩ ዩሐንስን አትስገድልኝ ሲል መገኘቱ ዮሐንስም በንጽሕናው እንደ መልአኩ ስለሆነ በማዕረግም መላእክትን ሊገዛ የሚችልበት ጸጋ ስለተሰጠው ይህን ሁሉ በመገንዘብ አንተም ሆንክ ባልንጀሮችህ ሐዋርያትና ነቢያት መጽሐፉንም የሚጠብቁ የእግዚአብሔር ፈቃድ ፈጻሚዎች ምዕመናን ጻድቃን ሰማእታት እንደ እኔው የምትቆጠሩ ስለሆነ ለበላያችን ለእግዚአብሔር እንስገድ በማለት ክብር እንደሰጠው ማእረጉን እንደገለጸለት እንጂ እንደወቀሰው ዕርማት እንደሰጠው አድርገን ከስህተት ማጥ ውስጥ እንዳገባን መጀመሪያ አትስገድልኝ ብሎ ከነገረው በኋላ ሁለተኛ መስገዱም ለመላእክት የጸጋ ሰጊድ እንደሚገባቸው ለማስተማር ያደረገው ነው እንላለን። መጀመሪያ ተሳስቶ ነው ከተባለ፣ ሁለተኛ መስገዱ የእንቢታ መሆኑ ነው፤ መላእክት ቃላቸውን ካላከበሩላቸው ወዲያውኑ እንደሚቀስፉ ቅዱስ ገብርኤል ዘካርያስን እስከተወሰነ ጊዜ ዲዳ አድርጎ እንደቀጣው በመመልከት መገንዘብ ይቻላል። /ሉቃ ፩ ቁ ፲፱-፳፫/

ዮሐንስ ለሁለተኛ ጊዜ ምክሩን ተላልፎ መስገዱን ያየ መልአክ ሳይቀስፈው ይተው ነበርን? ፊት በማስጠንቀቂያ አልፎታል፣ ለሁለተኛ ጊዜ ሲተላለፍ ለምን


## የሒሳብ አድራሻችን

ዋኖስ የሕትመትና
የማስታወቂያ ድርጅት
የተንቀሳቃሽ ሒሳብ ቁጥር
2152
ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ
አራዳ ቅርንጫፍ
ፖ. ሣ. ቁ. 32527
ስልክ 11 08 73
አዲስ አበባ


## እንኳን ደስ አላችሁ

በ1ኛ ዓመት ቁጥር አንድ መጽሔታችን በገባነው ቃል መሠረት በጥያቄዎች ውድድር ላሸነፋችሁት ደንበኞቻችን ሽልማታችሁን በአድራሻችሁ የምንልክ መሆኑን በደስታ እንገልፃለን ።

ሳይቀጣው ቀርቶ ፊትም በመስገዱ አለመሳሳቱን ኋላም መስገዱ በእንቢታ አለመሆኑን ስላወቀ የቅዱስ ዮሐንስን ክብር ለመግለጽ ብቻ የተናገረው ነው ብለን እናምናለን።

ሎጥ ለሁለቱ መላእክት በሰገደ፣ ጊዜ ኢያሱ ለቅዱስ ሚካኤል ሲሰግድ፣ ደቂቀ ያዕቆብ ለዮሴፍ፣ ናቡከደነጾር ለዳንኤል በሰገዱ ጊዜ አልተገሰጹም። ምክንያቱም በማዕረግ ስለሚያንሱ ትንሹ ትልቁን ማክበር ተገቢ መሆኑን ስላወቁ ነው። ዮሐንስ ግን በንጽሕናው እንደ መልአክ በማእርገ ክህነቱ ግን ከእነርሱ በላይ ስለሆነ፣ ምንም መምህር ትሕትናው ሆኖ ለእኛ አርአያ ሊሆን ለመልአኩ የጸጋ ስግደት ቢያቀርብለትም መልአኩ የዮሐንስን ቅድስናውን መንፈሳዊ ማዕረጉን ሊሰውር አልፈለገም። ስለዚህ ነበር አትስገድልኝ ያለው ከዚህ ውጭ ያለው ጉንጭ አልፋ ትርጓሜ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሥር የሌለው በዘፈቀደ የተተረጎመ ነውና አንቀበለውም።

ዕብ ፩ ቁ፲፬ መላእክት ሁሉ ረቂቃን አይደሉምን? የዘላለም ሕይወትን ይወርሱ ዘንድ ስለአላቸው ሰዎችስ ለአገልግሎት ይላኩ የለምን? ይላል እንጂ ለመላእክት የጸጋ ስግደት አታቅርቡላቸው አይልም። ከእግዚአብሔር ተልከው በተፈጥሮ ደካሞች የሆንነውን የሰው ልጆች እንደሚረዱን የሚያሳስበን ኃይለ ቃል ነው። ፍጹም ድኅነት አግኝተን መንግሥተ ሰማይን እስክንወርስ ድረስ ያግዙናል አገልግሎታቸውንም የሚፈጽሙት እኛን በመጠበቅ በማማለድ፣ በመራዳት በሥጋም በነፍስም በመታደግ ስለሆን የመላእክት እገዛ ያስፈልገናል። ተልእኳቸው ይህን በመሰለ ሁሉ ይከናወናል። ለነቢዩ ዘካርያስ የተገለጸለት መልአክ ስለ እግዚአብሔር ሕዝብ ሲያማልድ እንደነበረ በምልጃውም አማካይነት እግዚአብሔር ሕዝቡን በዓይነ ምሕረት የሚጎበኛቸው መሆኑን አብስሮታል። መላእክት በምልጃቸው ምሕረትን ከፈጣሪ በማስጠት አገልግሎታቸውን የሚፈጽሙ የሚረዱን ጠበቆቻችን ናቸው። /ዘካ ፩፣፲፪-፲፯/ ጌታም በሉቃስ ወንጌል የመላእክትን ተራዳኢነትና አማላጅነት በአት ክልት ሠራተኛው መስሎ ባስተማረው ምሳሌያዊ ትምህርት የመላእክትን አገልግሎት መገንዘብ እንችላለን። /ሉቃ ፲፫ ቁ ፮-፱/




www.ethiopianorthodox.org

መላእክት ሰዎችን በማገልገላቸው መከበር አይገባቸውም ለማለት የተጠቀሰ ከሆነም በውነቱ ታላቅ ስህተት ነው በመጽሐፍ ቅዱስ ክብር ያላቸው አገልጋዮች ናቸው «ነገር ግን ከእናንተ ታላቅ ሊሆን የሚወድ የእናንተ አገልጋይ ይሁን ከእናንተም ማንም ፊተኛ ሊሆን የሚወድ የእናንተ ባሪያ ይሁን እንዲሁም የሰው ልጅ ሊያገለግል ነፍሱንም ለብዙዎች ቤዛ ሊሰጥ እንጂ እንዲያገለግሉት አልመጣም» /ማቴ ፳ ቁ፳፮ ፳፰/ ማገልገል ለታላቅ ክብር እንደሚያበቃ ይህ የወንጌል ቃል ሊያስረዳን ይችላል። መላእክትም በማገልገላቸው ከክብር አይጎድልባቸው የበለጠ የጸጋ ስገድ ይቀርብላቸዋል እንጂ በዝቅተኛ ደረጃ አይታዩም ጥንቱንም በተፈጥሮአቸው ከሰው በላይ የሆነ ኃይልና ክብር አላቸው ደካሞች የሚረዱበት ምክንያት ትሑታንና የፈጣሪያቸውን ፈቃድ ፈጻሚዎች በመሆናቸው ነው። «ታስበው ዘንድ ሰው ምንድ ነው? ትጎበኘውም ዘንድ የሰው ልጅ ምንድር ነው? ከመላእክት እጅግ ጥቂት አሳንሳኸው» / መዝ ፰ ቁጥር ፬-፭/ መላእክት በተፈጥሮአቸው እንኳን ከሰው ብልጫ እንዳላቸው የተጠቀሰው የመዝሙር ቃል ብቻ ያስረዳናል በተፈጥሮዋቸውም ሆነ በአገልግሎታቸው ክብር ስለሚገባቸው ይህንኑ ዐውቀን የጸጋ ሰጊድ እናቀርብላቸዋለን።

፬ኛ/ ከጠያቂው «ታላቅነት ጻድቅነት ክብር የእግዚአብሔር እንጂ ፍጥረታት የሚቀራጩት አይደለም» ራእይ ፲፰፡፯-፰ «እራሷን ያከበረች የተቀማጠለች ንግሥት ነኝ ባልቴት አልሆንም ሃዘንም አላይም ያለች ተቀሰፈች ተቃጠለች።»

የሐዋ ሥራ ፲ -፳፮ እኔ ታላቅ ነኝ ያለውና የተከተሉት ሁሉ ሲጠፉ እናንባለን።

ሮሜ ፫፣ ፳፫-፳፭ «... ሰዎች ሁሉ ኃጢአት ሠርተዋል እግዚአብሔር የሰጣቸውንም ክብር አጥተዋል በእግዚአብሔር ጸጋ ብቻ ይጸድቃሉ እግዚአብሔር ይህን ማድረጉ የቀድሞውን ኃጢአት በመሻር የራሱን ጽድቅ መንገድ ለመግለጽ ነው» ይላል።

፬ኛ/ ከአዘጋጆች «የእግዚአብሔር ታላቅነት ጻድቅነት ክብር የባሕርይ ገንዘቡ ሲሆን በጸጋው ለፍጡራን የታላቅነትን የጻድቅነትን ክብር እንደአይነታቸው ጽናት እንደታዛዥነታቸው እያየ በለጋስነቱ የሚቸረው ስጦታ ነው። ፍጥረታት የእግዚአብሔርን ጸጋ አቃለው በራሳቸው ሥራ ተመክተው ታላቅነትን ጽድቅን ክብርን ሊያገኙ አለመቻላቸው የታመነ ነው የጸጋ ግን በሃይማኖትና በምግባር ተዋሕዶ ታላቅ ጻድቅ ክቡር አይባሉም። ይም ይህ አይታይላቸውም ማለት ሐሰት ነው ከመጽሐፍ ቅዱስ አንድም ቦታ ላይ አስረጅ አይገኝም በራእይ ፲፰ ቁ ፯-፰ ላይ የተጠቀሰው ስለ ታላቂቱ ባቢሎን ውድቀት የተነገረው። ከቁጥር ፪ እስከ ፮ ያለውንና ቁጥር ፱ና ፳ን ተመልከት።

በሐዋ ሥራ ፭ ቁ ፴፮ ላይ የተጠቀሰውም ቴዎደስ የተባለው ሰው በትዕቢቱ መጥፋቱን ያሳያል እንጂ ፍጡራን በጸጋ ታላቅ አይባሉም አይልም። በሮሜ ፫ ቁ ፳፫-፳፭ ላይ የተጠቀሰውም «ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋል የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሏቸዋል በማለት ሕዝብም አሕዛብም ተስተካክለው መደበላቸውን በኃጢአትም ምክንያት ጸጋ ክብር እንደጎደላቸው ከአስረዳ በኋላ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ለቤዛ ባፈሰሰው ደሙ በማመን ከኃጢአታቸው ነጽተው ከክብር ከጸጋ መድረሳቸውን ያሳያል እንጂ ለፍጡራን በሃይማኖታቸው በምግባራቸው ጸጋ አይሰጣቸውም አይልም። ሃይማኖት ያለምግባር ምግባርም ያለ ሃይማኖት ዋጋ እንደሌላቸው ያዕቆብ ሐዋርያ የገለጸውን መመልከቱ ይጠቅማል /ያዕ ፪ ቁ ፳፩-፳፮/ ።

ፍጡራን ታላቅ ጻድቅ ክቡር እንደሚባሉ በመጽሐፍ ቅዱስ በሰፊው ተዘርዝሯል «እግዚአብሔር ኖኅን አለው አንተ ቤተሰቦችህን ሁሉ ይዘህ መርከብ ግባ በዚህ ትውልድ ፊት ጻድቅ ሆነህ አይቼሃለሁና» /ዘፍጥ ፯ ቁ፩/ ይላል። እግዚአብሔር ኖኅን ጻድቅ ሆንሃል ብሎ መመስከሩ ጻድቅነትን ፍጡራን የሚቀራጩት ቢሆን አይደለምን? ቅዱስ ጴጥሮስም ሎጥን ጻድቅ ነው ብሎ መስክሮለታል የቅዱስ ጴጥሮስ ምስክርነት አይታመንምን? ካልታመነማ የአደረበት መንፈስ ቅዱስንም አይታመንም እንደማለት ይቆጠራል። /፪ኛ ጴጥ ፪ ቁ፯-፰/ እኛስ የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ አባታችንን ቅዱስ ጴጥሮስን ምስክርነቱን እንቀበላለን። ቅዱሳን በጸጋ በእምነታቸውና በምግባራቸው ጻድቅነት እንዳላቸው እናምናለን። ዳንኤል «ታላቁ አለቃ ሚካኤል ይነሣል» /ዳን ሉ፪ ፩/ ይላል ሚካኤል ታላቅነት ከሌለው ለምን በነቢያት ቃል ታላቅ ተባለ ነቢዩ ዳንኤል ሚካኤልን ታላቅ ማለቱ ከመንፈስ ቅዱስ ተረድቶ ታላቅነቱን ስለተረዳ አይደለምን ጌታችንስ «ከእናንተ ታላቅ ሊሆን የሚወድ የእናንተ አገልጋይ ይሁን» /ማቴ ፳ ቁ ፳፮/ ማለቱ በአገልግሎት /በትሕትና ሥራ/ ታላቅነት የሚሰጥ መሆኑን ወይም ፍጡራን የታላቅነትን ጸጋ ማግኘታቸውን ሲያበስር አይደለምን።

ስለዚህ ታላቅነት ለፍጡራን የሚሰጣቸው ጸጋ መሆኑን አስተውል። ቅዱስ ጳውሎስ «ክብር ለሚገባቸው ክብር ስጡ» /ሮሜ ፲፫ ቁ ፯/ ለምን አለ ለፍጡራን ክብር እንዳላቸው ሲያስገነዝበን አይደለምን? እንግዲህ ሰዎች በኃጢአታቸው በገዛ እጃቸው ክብራቸውን ያጣሉ እንጂ እግዚአብሔር በጸጋ ለፍጡራን ክብረን አጎናጽፎአቸዋል። ሰው ክብሩን በገዛ እጁ እንደሚያጣ ዳዊት እንዲህ ብሏል «ሰው ግን ክቡር ሆኖ ሳለ አያውቅም እንደሚጠፉ እንስሶች መሰለ» /መዝ ፵፰ ቁ ፲፪/

በሮሜ ፫ ቁ.፳፫ ላይ «ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋል» የሚለውን ብቻ ይዘው በሮሜ ፭ ቁ ፲፬ «በአዳም መተላለፍ ምሳሌ ኃጢአትን ባልሠሩት ላይ እንኳ ከአዳም እስከ ሙሴ ድረስ ሞት ነገሠ» ያለውን ሳትመለከት ቅዱሳንን ሁሉ ሠርተዋል ከማለት ተጠበቅ ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋል ሲል ከሕዝብም ከአሕዛብም ከሁለቱም ወገን ኃጢአት የሠሩ መኖራቸውን ሲያመለክት ኃጢአትን ባልሠሩት ላይ ሲል ደግሞ በአዳም በደል እንጂ በራሳቸው ኃጢአት ሞት ያልተፈረደባቸው ከኃጢአት ግብር ንጹሐን የሆነ ጻድቃን እንዳሉ ይመለከታልና ልብ ብለህ ተመልከት። ወንድማችን እንግዲህ እግዚአብሔር ማስተዋሉን ሰጥቶህ የአምልኮት ስግደት ለፈጣሪ ብቻ የጸጋ ስግደት ለቅዱሳን የሚቀርብላቸው መሆኑን እንድትረዳ እንመኝልሃለን። ከሚገባው በላይ ትኩረት በማድረግ ለጽሑፍህ ሰፊ ዐምድ ሰጥተነዋል። ሌሎች ሐሳቦችህ ግን ከስግደቱ ጋር ግንኙነት ስለሌላቸው አልፈናቸዋል።



www.ethiopianorthodox.org